# ለአድዋ መቶኛ ዓመት በዓል ለውድድር የቀረቡ ግጥሞች የአጻጻፍና የይዘት ትንተና

ፈቃደ አዘዘ

## መግቢያ

ባሁኑ ጊዜ በመገናኛ ብዙሃን በሚታተሙትና በሚሰራጩት ብዙ ግጥሞች ውስጥ ከአፃፃፍ ብልሃትና ከይዘት ጋር የተያያዙ ፕሮብሌሞች ይታያሉ። እነዚህን ግጥሞች የሚያነቡና የሚያዳምጡ ገጣሚዎችም የእነዚህን አቀራረብ እንደ መልካም አርአያ ቆጥረው ሲከተሏቸው ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት ውስጥ ተቋቁሞ የነበረው "የአድዋ ድል መቶኛ ዓመት በዓል አደራጅ ኮሚቴ" ላዘጋጀው የግጥም ውድድር በቀረቡት ግጥሞች ውስጥም ተመሳሳይ የቅርፅና የይዘት ፕሮብሌሞች አሉ። የዚህ መጣጥፍ ዋና ዓላማ እነዚህን ፕሮብሌሞች ማጥናትና መተንተን ነው። መጣጥፉ በተለይ በግጥሞቹ ድክመት ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል። ይህ የተደረገው ገጣሚዎቻችንን ለማስበርገግና ለመንቀፍ አይደለም። ግጥም ሲፅፉ አበክረው ሊያስተውሏቸው፥ ሊጨነቁባቸውና ሊመረምሯቸው የሚገቡ ነጥቦችን መጠቆም የግጥም አፃፃፍ ባህልን ያበለፅግ ይሆናል በሚል እምነት ነው። አንዳንድ አይነኬ ሆነው የቆዩ እሳቤዎችን በተመለከተ የሚነሱት ጥያቄዎችና የሚሰነዘሩት ሃሶቦችም ከአካዳሚያዊ ምክንያቶች ብቻ የመነጩ መሆናቸውን ለተመራማሪዎችና ለአንባቢያን ማስገንዘብ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም።

ለውድድር የቀረቡት 63 ግጥሞች በገፅ ብዛት 348 ነበሩ። ከነዚህ መሀከል፥ በሁለቱ ውስጥ የታየው መቀራረብ የመቀዳዳት ችግር እንዳለ ያለጥርጥር ስላመለከተ ሁለቱም ከውድድሩ እንዲወጡ ተደርጓል። ስለዚህ፥ ጥናቱ የተመሠረተው ባሁኑ ጊዜ በኢንስቲትዩቱ በሚገኙት 61 ግጥሞች ላይ ነው። የጥናቱ የመጀመሪያ ክፍል ታዋቂ ሀያስያን፥ ደራስያን እና ታሪክ ፀሀፊዎች፥ ታሪካዊ ጭብጥ ስላላቸው የፈጠራ ድርሰቶች አፃፃፍና ዓላማ፥ በተለያየ ወቅት የተናገሩትንና የፃፉትን ባጭሩ ያቀርባል። ይህ ለጥናቱ ትውራዊ ዳራ (theoretical background) እንዲሰጥ የታቀደ ነው። በሁለተኛው ክፍል ግጥሞቹ ሲጠኑ የተገኙት ዐበይት ፍሬነገሮች ይቀርቡና ጥናቱ በማጠቃለያ ያበቃል። በትንተናው እና በማጠቃለያው ውስጥ የተወሱት፡

ዐበይት ነጥቦች አንደኛ የወጣውን ግጥም (ግጥም ቁ.61) ምን ያህል እንደሚመለከቱ አነፃፅሮ ለማሳየት ሲባል ግን ኋለኛ (postscript) ታክሏል።

## 1. ትውራዊ ዳራ

የታሪካዊ ልቦለድን፥ የግጥምንና የተውኔትን አፃፃፍ የሚመለከት አንድ ወጥ ትውር አለ ለማለት ያስቸግራል። ልዩ ልዩ በሳል ሃያስያን፥ ደራሲዎች እና የታሪክ ፀሀፊዎች ግን ከምርምርና ከፈጠራ ድርሰት ልምዳቸው በመነሳት የተናገሯቸው፥ ብዙ ጊዜ በስነፅሁፍ-ሂስ መፃህፍትና ጆርናሎች ያቀረቧቸው ሃሳቦች አሉ። ከእነርሱ መሀከል፥ ከዓላማችን ጋር የተያያዙትን፥ የጥቂቶቹን ሀሳብ ለማቅረብ እንሞክራለን።

ብዙ ጊዜ ስለታሪካዊ ጭብጥና ስለፈጠራ ድርሰት ሲወሳ፥ ጦርነት እንዳንድ ጉልህ ነጥብ ይነሳል። ባንድ በኩል፥ ከታሪክ ፀሀፊዎች ማዕዘን ሲታይና ሲፃፍ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ታሪክንና የፈጠራ ድርሰትን አጣምረው በሚፅፉ ደራስያን ዓይን ሲታይና ሲፃፍ ልዩነት አለ። የሁለቱ ፀሀፊዎች አቀራረብና አመለካከት ይለያያል። ስለዚህ ታሪካዊ ጭብጥን (እንበል አንድን ጦርነት) ይዞ በሚነሳ የፈጠራ ድርሰት ውስጥ ደራሲው ምን ለማድረግ ቢሞክር ድርሰቱ በይዘትና በጥበብ የተዋጣ ይሆናል ስለሚለው ጥያቄ በተሠነዘሩት አስተያየቶች ላይ እናተኩራለን።

ሩሲያዊው ሀያሲ ቪሳርዮን ቤሊንስኪ ታሪክን የወታደራዊና የዲፕሎማሲያዊ ዜና መዋዕል አድርገው የሚቆጥሩትን የታሪካዊ ድርሰት (ልቦለድ) ፀሀፊዎች አሉታዊ በሆነ መንገድ ይተቻል። ትውልድ በተለዋወጠ ቁጥር የልማድና የባህል ለውጥ መከተሉን ጠቅሶ፥ እነዚህ ለውጦች ከውሎችና ከጦርነቶች ታሪክ ይበልጥ እንደሚስቡ የዛሬ መቶ ሀምሳ ዓመት ገደማ ፅፏል (in Hayden: 379-380)። በሁላችንም ዘንድ እንደሚታወቀው ጦርነት ውጊያ ብቻ አይደለም። ነገሩ የጥይት መተኮስ፥ የጋሻ መመከት፥ የጦር መወርወር ወይም በዘመናዊ ጦርነት በ"ማሽንገን" የማጨድ፥ በአውሮፕላን የመለሽለሽ ጉዳይ ብቻ አይደለም። እርግጥ የአካል መቁሰል (ማቁሰል፥ መሞት) መግደል ገናኑ ጉዳይ ሆኖ ብዙ ጊዜ ይወሳል። በዚህ በመግደል-መሞት ሂደት ውስጥ ግን በተሳታፊዎቹ ህሊና ውስጥ የሚካሄድ የሀሳብና የስሜት ሞገድ አለ። ስለራስ ዕጣ ፈንታ፥ ስለልጆችና ሚስት፥ ስለዘመድና ወገን እያሰበ እያንዳንዱ ተዋጊ ስላለበት ሁኔታ፥ እዚያ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንደገባ እያሰበ፥ "ልክ ነኝ? ልክ አይደለሁም?" እያለ እየተጨነቀ፥ እየፈራ፥ እየደፈረ በዚህ ዓይነት መዋግደ ህሊና ውስጥ ሆኖ ነው የሚሞት-የሚገድል። ረሀቡ፥ ጥማቱ፥ እርዛቱ፥ ውርጩ፥ ሙቀቱ፥ ጣመኑ፥ በሽታው፥ ስቃዩ ደግሞ አካሉን ይተገትገዋል። ከዚህ ሌላ ጦርነት በኢኮኖሚ፥

በፖለቲካና በማኅበራዊ ኑሮ ላይ ችግርና ለውጥ ያስከትላል፡፡ በጠቅላላ የማኅበረሰቡ መዋቅር ይታመሳል፥ ይዋዥቃል፥ ይናጋል፡፡ ለበጎ ሰብአዊ ዓላማና ምክንያት በጀግንነት እስከ መስዋዕትነት ቆርጦ የሚታገለው፥ ለሥልጣንና ለጥቅም ሲል ጦርነቱ ውስጥ የሚገባው፥ በጦርነቱ በቀጥታ ከመካፈል ራሱን አድኖ ከጦርነቱ በሚመነጩ ልዩ ልዩ ችግሮች ይሉኝታውንና ነፍሱን ሸጦ የሚነግደው፥ ጦርነቱና ጦርነቱ ያስከተላቸው ለውጦች ግራ አጋብተውት የሚዋዥቀው፥ የዘመተ ባላቸውን፥ ልጃቸውን፥ ዘመዳቸውን እያሰቡ የሚፀልዩና የሚያነቡ ብዙኀን፥ ወዘተ. የእነዚህ ሁሉ ህይወት ይታመሳል፡፡ ስግብግብነትና አውሬነት ባንድ በኩል፥ ሰብአዊነት (humaneness) በሌላ በኩል በልዩ ልዩ ደረጃና በልዩ ልዩ ምክንያት በህይወት ውስጥ እየተከሰቱ ህይወትን ያምሳሉ፡፡

ስለዚህ ታሪካዊ ጭብጥ ያለው ግጥም፥ ተውኔት፥ ልቦለድ እፅፋለሁ የሚል ደራሲ ጥበባዊ ክሂሉንና ዕውቀቱን የሚፈታተኑ ብዙ ጉዳዮች ያጋጥሙታል ማለት ነው፡፡ በእነዚህ የሥነፅሁፍ ዘርፎች መሀከል ያለው ልዩነት ታሪካዊ ጭብጥን የሚያቀርቡበትንም መንገድ የተለያየ ያደርገዋል፡፡

በእያንዳንዱ ዘርፍ ሲፅፍ ደራሲ የሚያጋጥመው ችግርና መፍትሔ ብዙ ጊዜ የተለያየ ነው፡፡ ዋናው ልዩነታቸው፥ የታሪካዊ ልቦለድ ደራሲ ዝርዝር ታሪካዊ ጉዳዮችን ለማካተት ሰፊ ቦታና ጊዜ ያለው መሆኑ ነው፡፡ እንደልቦለድ ደራሲውም ባይሆን፥ ፀሀፌ-ተውኔቱም በመድረክ ገፆች፥ በአልባሳት፥ በቁሳቁሶችና በሌሎች ቴክኒኮች አማካይነት መልካም ታሪካዊ ድራማ ማቅረብ ይችላል፡፡ የገጣሚው ሁኔታ ግን ከእነርሱ የተለየ ነው፡፡ ረዥም የኤፒክ ግጥም ልፃፍ ካላለ በቀር፥ የልቦለድ ደራሲው ባንደኛ ደረጃ፥ የተውኔት ደራሲው በሁለተኛ ደረጃ፥ ያላቸውን ሰፊ ቦታና ጊዜ እርሱ የለውም፡፡ ገጣሚው፥ በተቻለ መጠን፥ በተመጠነ ቦታና ጊዜ ትልቅና ጥልቅ ሀሳብን ለማስፈር እንዲሞክር ይገደዳል፡፡ ጥበባዊ ጉዳይን የሚመለከቱት ፕሮብሌሞች ግን የጋራቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ደራሲው፥ ጦርነቱ በሰዎች ህይወት ላይ ያስከተላቸውን ለውጦችና የለውጦቹን መነሻዎችና ማጠንጠኛዎች <u>የሰው ልጆች ኑሮ</u> አድርጎ ነው መፃፍ ያለበት <u>ወይስ</u> የጦርነት ፍልሚያዎች የተካሄዱባቸውን ቦታዎች፥ የተዋጊዎቹን መሪዎች ስሞች፥ የዲፕሎማሲያዊ ውሎች፥ ወዘተ. ዝርዝሮች ማጠንጠኛ አድርጎ በጥሩ ቋንቋ የታሪክን ቅደም ተከተል ተከትሎ ነው መፃፍ ያለበት፡፡ የእርሱ ጉዳይ የማን ጦር በየት በኩል ዘምቶ ስንት እንደገደለ፥ ስንት እንደሞተበት መዘገብ ነው? ወይስ ከፍ ብለን ያነሳናቸውን ሕይወታዊ

ጉዳዮች በምላታቸው መሳል ነው? ይህ አንዱ፥ ዋነኛውም ማለት ይቻላል፥ ጥበቡን የሚፈታተን መሠረታዊ ፕሮብሌም ነው።

የሁንጋሪያ ተወላጅ የሆነው የሥነፅሁፍ ሀያሲው ጆርግ ሉካሽ ይህንን እና ተመሳሳይ ፕሮብሌሞችን በጥልቀት በመረመረበት *The Historical Novel* በሚለው መፅሀፉ የሚከተለውን አበክሮ ይናገራል፤

> What matters . . . in the historical novel is not the re-telling of great historical events, but the poetic awakening of the people who figured in those events. What matters is that we should re-experience the social and human motives which led men to think, feel and act just as they did in historical reality. And it is a law of literary portrayal which first appears paradoxical, but then quite obvious, that in order to bring out these social and human motives of behaviour, the outwardly insignificant events, the smaller (from without) relationships are better suited than the great monumental dramas of world history . . . (Lukacs, 1962:42)

በጥቅሱ አማካይነት ሊያስረዳ የሚሞክረው፥ የልቦለድ ደራሲው ዋና ተግባር ታላላቅ ታሪካዊ ሁነቶችን መልሶ መተረክ አለመሆኑን፤ ሰዎች ባንድ ታሪካዊ ወቅት በሆነ መንገድ እንዲያስቡና እንዲተገብሩ ያደረጓቸውን ማኅበራዊና ግላዊ ግፊቶች አንባቢዎች እንዲያውቋቸውና፥ ያለፈው ዘመን ህይወት ዛሬ ለእነርሱ እንዲሰማቸው ማድረግ መሆኑን፤ እና ላይላዩን ሲመለከቷቸው ፋይዳቢስ የሚመስሉ ታሪካዊ ሁነቶች ደግሞ ታላላቅ ከሚባሉት በዓለም ታሪክ ውስጥ ከተከናወኑ ሁነቶች ይበልጥ እነዚህን ማኅበረሰባዊና ሰብአዊ ግፊቶች ለመሳል እንደሚያመቹ ነው። ሀሳቡን ከታሪካዊ ልቦለድ ጋር አያይዞ ያነሳው እንጂ፤ ጥበብ-ነክ የሆነው ነጥብ፥ ታሪካዊ መረጃዎችን በዝርዝር ማኅጎድጎድ የደራሲው ጉዳይ አለመሆኑን አበክሮ መግለፅ ነው። በጦርነቱ ውስጥ ለተከሰቱት ሁኔታዎች መነሻ የሆኑትን ጥልቅ፤ ረቂቅና ስውር ምክንያቶች እሰዎች ህሊና ውስጥ ጠልቆ ገብቶ ለመረዳት መጣር ግን የጥበቡ ዋና ተልዕኮ (artistic mission) ነው። ሉካሽ አጠንክሮ የሚናገረው፥ ደራሲው፥ የመረጃ ድርደራውን ለብዙው የታሪክ ፀሀፊ ትቶ፥ ብዙው የታሪክ ፀሀፊ ችላ ያለውን የሰውን ልጅ ልብና ህይወት ( the human heart and life) መመርመር ላይ ያተኩር ነው (1962:42)።

ፕሮስፐር ሜሪሜ (Prosper Merimée) የተባለው የፈረንሳይ ደራሲ ደግሞ ታሪክን መርምሮ፥ ከውስጡ ለሰው ልጆች ሁሉ፥ ለሁልጊዜ የሚጠቅም ምግባራዊ ትምህርት ጨምቆ ለማውጣት ስለሚፈልግ በታሪክ ጥናት ላይ እንደሚያተኩር ይናገራል። ከታሪክ በጣም የሚወደውም ልዩ ልዩ አጫጭር ትርክቶችን (anecdotes) እንደሆነ ይገልፅና ለዚህ ምርጫው ዋናው ምክንያት፥ እነርሱ ውስጥ የአንድን ዘመን ትክክለኛ ገፅታ አገኛለሁ የሚል እምነቱ መሆኑን ይናገራል። ይህንን የሜሪሜን ምርጫ አስታኮ ጆርግ ሉካሽ የሚከተለውን ፅፏል፤

> For this reason memories have more to offer him than historical works, for they are intimate conversations between author and reader and hence give a picture of the age that has all the closeness and intimacy of direct observation, which Merimée (like Vitet) sees as the decisive factor in the presentation of history . . . (1962:80).

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ሜሪሜ ድርሰቱን ከመፃፉ በፊት እንደግል ገጠመኝ ስሜትና አእምሮን የሚነኩትን ትርክቶች ይመረምራል፥ ያጠናል ማለት ነው።

<u>የዌቨርሊ ልቦለዶች</u> <u>(The Waverly Novels)</u> በተባሉት ታሪካዊ ልቦለዶቹ በዓለም ላይ ዝናን ያተረፈው ዋልተር ስኮትም ከታሪክ ዕሁፎችና ከትውስታዎች ስለሚፈልገው ነገር ሲናገር እንዲህ ይላል፤

> I began . . . to seek in history, memoirs, voyages and travels and the like, events nearly as wonderful as those which were the work of imagination, with the additional advantage that they were at least in a great measure true (quoted in Grierson, 1950:38).

የስኮት የቅድመ ድርሰት አንዱ ስልት፥ የታሪክ መዛግብትን፥ የጉዞ ዘገባዎችንና የመንገደኞችን አስተውሎቶች፥ ትውስታዎች መመልከት ነው። ይህንን የሚያደርገው ግን፥ እንደ ታሪክ ፀሀፊ ደረቅ መረጃዎችን ለመሻት ሳይሆን በምናባዊ ሥራዎች ውስጥ የሚገኙትን ዓይነት አስደናቂ ('አስወንዳሪ'ም ቢባል አይከፋም) ነገሮች ለማግኘት ነው። በመዛግብት የሠፈረውን ይመለከታል እንጂ ያገኘውን ሁሉ አያግበሰብስም ማለት ይመስላል። ልዩና ትንግርታዊ ነው የሚለውን ግን ለይቶ አውጥቶ በዚያ አማካይነት የዘመኑን ወረራ (sprit of the age) ይመለከትበታል። በዘመኑ፥

ታሪካዊ ልቦለዶቹ ብዙ ጊዜ የሚወደዱና ህይወት ህይወት የሚሸቱ መሆናቸው በሰፊው ይነገራል። ይህ የሆነበት አንድ ምክንያት የታሪክ ዕውፎችን ከሚገለገልበት መንገድ መንጭቷል ማለት ይቻላል።

የስኮትን ታሪካዊ ልቦለድ በጥልቀት የመረመረው ሉካሽ የደራሲውን ልዩ ችሎታና አዲስ አቀራረብ ሲገልፅ የፃፈው ደግሞ እንደ አንድ ሌላ መሠረታዊ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል።

> Scott portrays the great transformations of history as transformations of popular life. He always starts by showing how important historical changes affect everyday life, the effect of material and psychological changes upon people who react immediately and violently to them, without understanding their causes . . . . (Lukacs:49)

ታላላቅ ታሪካዊ ለውጦች በዘለለታዊው የሕዝብ ኑሮ ላይ የሚያስከትሏቸውን ለውጦች እየሳለ ስለሚፅፍም የስኮት አፃፃፍ ትኩረት፥ ከታሪክ ኳንታዊና ኳልታዊ (quantitative and qualitative) መረጃዎች ዘገባ በጣም የዘለለ መሆኑን በይበልጥ ያስገነዝባል። ሄንሪ ጀምስ የተባለው የልቦለድ ደራሲ የስኮትን ሥራዎች ሲያደንቅ፥ ከግጥም ድርሰት ውጭ ሰዎች ኑሯቸውን ሲኖሩ ባህርያቸው እየተሳለ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረቡት በስኮት ልቦለዶች ነው ማለቱም ለስኮት የአፃፃፍ ዘዴ ሌላ ትልቅ ምስክርነት ነው (in Hayden:429)።

ከዚህ በላይ የሁለት ሀያስያንን እና የሁለት የታሪካዊ ድርሰት ፀሀፊዎች አስተያየት ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የሁለት የታሪክ ጸሐፊዎችን አስተያየት ባጭሩ እንገልፃለን። ካርላይል (Carlyle) ታሪካዊ ልቦለዶች ለታሪክ ጥናት ከፍተኛ ዋጋ አላቸው ብሎ ያስባል። በመሠረቱ፥ የሚያነሳቸው ነጥቦች ሀያስያኑም ሆኑ የልቦለድ ደራሲዎቹ ከሚያነሷቸው የተለየ አይደለም። ነገር ግን በፀሀፊ ታሪኩ አንደበትና አቀራረብ ነጥቡን ለማቅረብና ነጥቡን ለማጠናከር ስንል ባጭሩ እንጠቅሰዋለን።

> . . . Historical novels have taught all men this truth . . . that the bygone ages of the world were actually filled by living men, not by protocols, state papers, controversies and abstractions of men. Not abstractions were they, not diagrams and theorems, but men, in buff or other coats and breeches, with colour in their cheeks, with passion in their

stomach, and the idioms, features and vitalities of very men (in Grierson: 42-43).

የልቦለድ ድርሰቶች የሰዎችን አለባበስ፥ መልክ፥ ውስጣዊ ስሜት፥ የአነጋገር ዘየና የሕይወት ትርታቸውን ስለሚስሉ ያላቸውን እሴት ካርላይል አበክሮ ያመለክታል። ሌላው ታሪክ ፀሀፊ ማካውሌ (Macaulay) ደግሞ ከ19ኛው ክፍለ ዘመንና ከዚያም በፊት የነበረው የታሪክ አፃፃፍ የሕዝቦችን ሕይወታዊ ታሪክ በመፃፍ ፋንታ የወረራ፥ የጦርነቶች፥ የቤተመንግሥት መፈንቅለ መንግሥቶች፥ የአስተዳደርና የዲፕሎማሲ ታሪክን በመፃፍ ላይ ማተኮሩን ሂሶ "ምሉእ ታሪክ" ("Complete history") የመፃፍን አስፈላጊነት አጠንክሮ ይናገራል (Macaulay's: 100)። እርሱ ያሰበው ዓይነት ታሪክ ስለሚፃፍበት ሁኔታ ሲናገር ከሚያነሳቸው ዋና ነጥቦች አንደኛውን ሲገልፅ፥ ". . . a truly great historian would reclaim those materials which the novelist has appropriated" (in Macaulay's:158) ይላል። ይህ፥ የአድዋ ጦርነት ከመዘመቱ 60 ዓመታት ቀድሞ የተነገረ ልብ ሊባል የሚገባ ነጥብ፥ የኢትዮጵያን ታሪክ ተሚፅፉ ሰዎች ልብ ደርሷል የሚያስብል ሥራ ለማየት እንደጓጓን አለን።

ደራሲዎቻችን በታሪካዊ ጭብጦች ላይ ተመሥርተው ልቦለዶች፥ ተውኔቶች እና ግጥሞች ለመፃፍ እንደሞከሩ ይታወቃል። እነዚህን በሙሉ አጥንቶ ለመፃፍ የሞከረ ጥልቅ ሥራም ገና ስለሌለ ስለእነርሱ በዝርዝር ለመናገር አንቃጣም። ያነበብናቸውን መሠረት አድርገን በጥቅሉ እንናገር ካልን ግን፥ ወደስኮትና ወደሜሪሜ፥ እና፥ ባልዛክ "የተፈጥሮ ታሪክ ፀሀፊ" ("the historian of nature") [in Hayden (ed):377] ወደሚለው ወደ አሜሪካዊው የኩፐር ልቦለዶች ዘንድ ለመጠጋት የሚያዘግሙበት ደረጃ ላይ እንኳን ገና የደረሱ አይመስሉም። እርግጥ፤ ይህ አነጋገር፥ ከፍ ብለን እንደጠቆምነው፥ ሊደገፍም ሆነ ሊነቀፍ የሚችለው በበሳል የሥነፅሁፍ ሂስ፥ ድርሰቶቹ ሲመረመሩ ነው። ስለዚህ አጠቃላዩን የሀገራችንን ታሪክ ቀመስ ድርሰቶች ጉዳይ ለጊዜው ትተን ለአድዋ ድል መቶኛ ዓመት ለውድድር የቀረቡትን ግጥሞች ባጭር ባጭሩ እንገመግማለን።

## 2. የውድድር ግጥሞች ትንተና

በግጥሞቹ ላይ የሚደረግ ዝርዝር ጥናት በአንድ አጭር መጣጥፍ ሊካተት አይችልም። ምክንያቱም ግጥሞቹ የተፃፉት በ61 የተለያዩ ገጣሚዎች ነው።

እያንዳንዱ ገጣሚ የራሱ የአፃፃፍ ዘየ÷ ርእሰ ትኩረት እና አመለካከት አለው:: በዚህ ላይ ግጥሞቹ 340 ገፆች ላይ የሰፈሩ ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ ዝርዝር ማስረጃ እየጠቀሱ÷ የተስተዋሉትን ነጥቦች ሁሉ መተንተኑ አስቸጋሪም÷ ቦታም የሚፈጅ ነው:: ስለዚህ በ'መግቢያ'ችን እንደጠቆምነው÷ ገናን እና ጉልህ በሆኑት ከአፃፃፍ እና ከይዘት ጋር በተያያዙት ፕሮብሌሞች ላይ ብቻ እናተኩራለን:: ግጥሞቹን በይበልጥ ለመመርመር የሚፈልግ ተመራማሪ ግን ወደ ኢንስቲትዩቱ ቤተመፃህፍት እንዲያመራ እንጠቁማለን::

## 2.1 ከአፃፃፍ ጋር የተያያዙ ፕሮብሌሞች

ለውድድር ከቀረቡት ግጥሞች መሀከል ከ75% የማያንሱ ተራ ትረካና ተራ ስድ ንባባዊነት ጎልቶ ይታይባቸዋል:: ከውጫሌ ውል አንቀፅ 17 ጀምረው እስከ አድዋ ጦርነት ፍፃሜ ድረስ የተከናወኑትን ድርጊቶች በገባቸውና በመሰላቸው መንገድና ቅደም ተከተል የሚያቀርቡ÷ አሰልች ተራኪ ሊባሉ የሚችሉ ግጥሞች አሉ (ቁ 06፣ ቁ.10፣ ቁ. 34፣ ቁ. 56ን ለአብነት መመልከት ይቻላል):: ለየት ያሉ ተራኪዎችም አሉ:: ከላይ እንደጠቀስናቸው በጣም ባያሰለቹም እነዚህም የአንባቢን ስሜት የመሳብና ይዞ የማቆየት አቅም የሌላቸው ናቸው:: ጣሊያኖች ያመረቱትን ምርት የሚጥሉበት ቦታና ለኢንዱስትሪዎቻቸው ጥሬ ዕቃ ፍለጋ ከሀገራቸው ወጡ ብለው ጀምረው÷ በውጫሌ ውልና ሀገር ውስጥ በነበረው የኢትዮጵያ መሪዎች አለመግባባት በኩል እስከ አድዋ ድል የተገነዘቡትን የሚደረድሩ ናቸው:: ትረካቸው ፍዝ ነው:: ሕሊናን የሚያነቃቃ አይደለም (ቁ. 04፣ ቁ. 41 ይመልከቱ):: ችግሩ ግጥሞቹ ተራኪ እመሆናቸው ላይ አይደለም:: ለምሳሌ÷ የመንግሥቱ ለማ "ባሻ አሸብር በአሜሪካ" እና በታሪክና ምሳሌ ውስጥ ያሉት ብዙዎቹ የከበደ ሚካኤል ግጥሞች ተራኪ ናቸው:: እነዚህ ግጥሞች በቋንቋቸው÷ በለዛቸው÷ በአተራረክ ስልታቸው ማራኪነት በጣም ይለያያሉ:: የውድድር ግጥሞቹ ቋንቋና የአተራረክ ስልት ግን ተራ በመሆኑና ሥርዓታዊ አካሄድም ስለሌለው ነው አሰልች እና ፍዝ የሚሆነው::

ብዙዎቹ ግጥሞች ዳርግጥም ሊባሉ የሚገባቸው ናቸው:: ዳርግጥም በንል፣ የስንኞቻቸውን የመጨረሻ ሆሄዎች ብቻ 'ን÷ን'÷ 'ጉ-ጉ' 'ድ-ድ' ወዘተ እያደረጉ የሚገጥሙ÷ ተሯ ስድንባባዊነት መለዮአቸው የሆነ÷ ሙዚቃዊና ዘይቤያዊ ውበት የሌላቸው÷ በያዙት ሀሳብ ጥልቅና ረቂቅ ምናብን የማይማርኩ ግጥሞች ማለታችን ነው::

ከመረብ ወንዝ ባሻገር ያስተዳድር የነበረውን
ያን ታላቁን ጀግና አሉላ አባ ነጋን

በተለያየ ሁኔታ ገፀበረከት በመስጠት
ጦሩን እንዲከድ እንዲሁም ዜግነት
ሞክራ ነበር እንግሊዝ ወጥሯት ትዕቢት
(ቁ.24÷ ገፅ 1-2)

እንዲህ ብቅ ስትይ በዓመትሽ
አድዋ ድስ [sic] ማለቱ ቀንሽ
ዓመት ቆይተሽ ሳይሽ
አስራ ሁለት ወራትን አስቆጥረሽ
ብቅ ትያለሽ÷ አንድ ዓመት ሆነሽ
አድዋ ዘላለም እንቁ ነሽ
አድዋ ዘላለም እንቁ ነሽ (ቁ.44÷ ገጽ1)

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ምሳሌዎች ማንኛውም በሕይወት የሚንቀሳቀስ ሰው÷ ቤት መምቻዎቹን ብቻ እያገጣጠመ ሊፅፋቸው ይችላል:: ስንኞቹ ምናብን የሚያነቃቃ÷ የሚተነኩስ÷ የሚኀነትል ይዘትም ሆነ ስሜት የላቸውም:: ቋንቋቸውም ቢሆን ተራ ነው:: ሀሳቦቹም ቢሆኑ ፊት ለፊት÷ በዘለለታዊ ተራ ምልልስና ውይይት በሚቀርቡበት መንገድ የቀረቡ እንጂ ወጥነት (originality) ባለው መንገድ የተሰነዘሩ አይደሉም::

ብዙዎቹ ያማርኛ የጋዜጣ፡ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ግጥሞች ውስጥ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ግጥሞች በሽበሽ ናቸው::

እንደምን አላችሁ
አድማጮቼ ናችሁ
ከእኔ ወዳጃችሁ
የሚቀርብላችሁ
ፕሮግራም አላችሁ
ስሙኝ እባካችሁ
በመጀመሪያ ግን
ሙዚቃ ይህችን
ከስክሱ እባካችሁ፤

የሚሉ ዓይነት ግጥሞችና ጸሀፊዎቻቸው ክብር አግኝተው በየመድረኩ ላይ ስለነገሡበት÷ ወጣቱና ሌላው አድማጭ እነርሱን እንደመመዘኛ ቆጥሮ (እርሱ እንኳን አይፈረድበትም) በነርሱ ፈር መግጠም በጀመረባቸው ባለፉት ከ20 የማያንሱ ዓመታት÷ እነዚህ ስድ ዳርግጥሞች እየተስፋፉ ሄደዋል:: የመንግሥቱ ለማ÷ የፀጋዬ ገ/መድኅን÷ የዮሐንስ አድማሱ÷ የገብረ ክርስቶስ

ደስታ፥ የሰሎሞን ዴሬሳ፥ የሰይፉ መታፈሪያ ወዘተ ግጥሞች በተላለፉበት ሬዲዮ፥ በሚያስገመግም የገደል ማሚቶ እየታጀቡ የ"ትትት-እና-ድድድ" ግጥሞች ተንሠራፍተው መገኘት የአብዛኛውን ወጣት እና የሌላውን አድማጭ የጥበብ ማጣጣም ክሂል አዶልዱሞታል ማለት ይቻላል። የባህል እድገት ያገባናል የሚሉ፥ በተለይም የመገናኛ ብዙሀንን የሚያስተዳድሩ የአበውን እና የወጣት ገጣምያንን ምርጥ ግጥሞች እያሰሙ የተጠቀሱትን ድክመቶች ለማሻሻል ካልረዱ ሁኔታው ሊባባስ ይችላል። ፕሮብሌሙን ከአማርኛ ግጥም ታሪክ እና ሂስ ጋር አያይዞ በዝርዝር መመርመርና ውጤቱንም በይፋ መግለፅም የባለሙያዎች ግዴታ ይመስለናል።

ሌላው ነጥብ ብዙዎቹ ግጥሞች በተለመዱና በላሸቁ ዘይቤዎች የተፃፉ መሆናቸው ነው። የአድዋ ጀግኖች ከአውሬዎች ያው ከአንበሳ፥ ከነብር፥ እና ከግስላ ጋር፤ ከተፈጥሮ ክስተቶችም ከማዕበል፥ ከሞገድ፥ ከዶፍ ዝናብ፥ ከሰደድ እሳትና ከበረዶ ዝናም ጋር ነው የሚነፃፀሩት። የጠላት ወታደርም "ቀንድ የለሽ በሬ"፥ "ነጫጭባ"፥ "ፋሽሽት"፥ "ሶላቶ" ተብሎ ነው የምናነበው። ብዙዎቹ አዳዲስ ዘይቤዎች ለመፍጠር አይጥሩም። የአንዳንዶቹ ሙከራም ከልብ የሚያስቅ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ ያህል፥

እንጻፍ ግጥም የቀላ
በደም እንጂ መች በሳልሳ (ቁ. 26፥ ገፅ 15 ሥርዝ የኔ)

የሚለውን እና

አንቺነትሽ . . . ዘመን ቆርጦ፥ አቆራርጦ
የጊዜ ድንጋይ ፈንቅሎ፥
የታሪክ ቢጫ ሲያሣየኝ፥
የያኔውን ሲመግበኝ፥ (ቁ. 23፥ ገፅ 2፥ ሥርዝ የኔ)

የሚሉትን መጥቀስ ለጊዜው ይበቃናል።

ታሪካዊ ጭብጥ ባለው የፈጠራ ድርሰት ውስጥ ያለፈን ዘመን ቋንቋ ምን ያህል መከተል፥ ምን ያህሉን ማስታወስና መቅዳት ይቻላል? የሚል ጥያቄ በባለሙያዎች ዘንድ ይነሳል። ቀለል ያለ መፍትሄ ከሚመስሉን የዋልተር ስኮት ሀሳብ ይገኝበታል። በእርሱ አስተያየት ቋንቋውን በአያቶች ቋንቋ በማድረግ ድርሰቱ ታሪካዊ ቃና እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል። ከራስ ዘመን ቋንቋ ለየት ያለ ቃና መስጠት ስላለፈው ዘመን ቅምሻ ለመስጠት ያህል ይበቃል። የቀረውን በገለፃዎች፥ በገፀባህርያት አሳሳል፥ በሰዎች ጠባይና አመል አቀራረፅ ለማሟላት መሞከር እንደሚያስፈልግ መጠቆሙንም

ግሪየርሰን ተናግሯል (in Grierson: 42):: ግጥም ብዙ ጊዜ የልቦለድን ያህል ሰፊ ጊዜና ቦታ ስለማይኖረው ለተለያዩ ሀሳቦችና ስሜቶች ታሪካዊ ቃና ለመስጠት ዕድል የለውም ማለት ይቻላል:: ስለዚህም ብዙው ገጣሚ በራሱ ዘመን ቋንቋ ይፅፋል::

በውድድሩ ግጥሞች ውስጥ ሌላ የቋንቋ አጠቃቀም ይታያል:: ገጣሚዎቹ የራሳቸውን ዘመን አባባሎች በአድዋ ዘመን የነበሩ ድርጊቶችን መግለጫ ሲያደርጉ ይገኛሉ:: ለምሳሌ፥ ህዝቡ "ከዘላለም ባርነት ያንድ ቀን ነፃነት" ብሎ ተነሳ የሚለው በዘመነ ደርግ ተደጋግሞ ይሰማ ከነበረው የተወሰደ ይመስላል:: በዘመነ ኢህአዴግ ቃና ደግሞ "ጦር መሥራት ቁብ የለሾች ለሆነልን ሙዚቃ" እና "ሰላምን በመርገጥ . . ." (ቁ. 39፥ ገፅ 02) የሚሉት ይገኛሉ:: የኮሎኔል መንግሥቱን አባባልና ሀሳብ ነጥቆም፥

ኢትዮጵያዊው ጦር በአድዋ ሲሠፍር
ለአፍሪካ ምድር ይበቃ ነበር (ቁ. 17፥ ገፅ 06)

ያለም አለ:: ይኸው ገጣሚ፥ ከጦርነቱ በኋላ ብዙው የጠላት ጦር በአድዋ ላይ በጎራዴ ሲያልቅ "የተረፈው ገባ ቀይ ባህር" ሲልም የዘመነ ደርግን ቋንቋና ዘይቤ ይዞ እንደሚፅፍ በይበልጥ እንረዳለን::

የቦታዎችና የሰዎች ስሞች ማብዛትም አንዱ የግጥሞቹ ባህርይ ነው ማለት ይቻላል:: ግጥማዊ ውበትን ከቁም ነገር ሳያስገቡ፥ ለፖለቲካዊ ክርክር ማሳመኛ ሲሉ ብቻ የጀግኖችን ስሞች ከየብሔረሰቡ የሚደረድሩ አሉ:: ያለምንም ቴክኒካዊ ፋይዳ የጦርነት አውድማዎችን የሚዘረዝሩም አሉ:: የአንባቢውን ስሜት ማርከው ለማቆየት የማይችሉ ደረቅ ገለፃዎች ናቸው:: ዕንባ-ጠገብ፥ አሰልቺ፥ ተደጋጋሚና ስሜት የማይኮረኩሩ ውዳሴዎችን አወዳሽ ቅፅሎችና የፈረስ ስሞች በመደርደር ማቅረብም አንዱ ባህርያቸው ነው:: ይህ ሁሉ፥ ከገጣሚዎቹ ክሂል ደካማነትና፥ በትውራዊ መግቢያችን የተመለከቱትን ጉዳዮች ለማጤንና ለመመርመር አቅሙም፥ እድሉም፥ ፍላጎቱም የሌላቸውና በድፍረት የሚጫጭሩ ከመሆናቸው የመነጨ ሳይሆን አይቀርም:: ምናልባት የዮፍታሔን ስንኞች፥ አፅሙን ይቅርታ ጠይቀን፥ ለማንፀሪያ ያህል ብንጠቅስ ምን ማለታችን እንደሆነ ይበልጥ ግልፅ ይሆን ይሆናል::

ፋሽሽት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በ1928 መውረሯ እንደተረጋገጠ፥ ዮፍታሔና ሌሎች ገጣሚዎች ሕዝቡን ለመቀስቀስ ግጥሞችና መዝሙሮች ይፅፉ ነበር:: ብዙ ጊዜ ከሚጠቀሱት የዮፍታሔ ስንኞች ጥቂት እንጠቅሳለን::

አጥንቱን ልልቀመው መቃብር ቆፍሬ
ጎበናን ከሸዋ አሉላን ተትግሬ
ስመኝ አድሬአለሁ ትላንትና ዛሬ
አሉላን ለጦይት ጎበናን ለጭሬ
ተሰባሰቡና ተማማሉ ማላ
አሉላ ተትግሬ ጎበና ተጋላ
ጎበና ሴት ልጁን ሊያስተምር ፈረስ
አሉላ ሴት ልጁን ጦይት ሊያስተኩስ
አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ
ነገራችን ሁሉ የእንቧይ ካብ የእንቧይ ካብ

(ዮሐንስ፥ ገፅ 204)።

ዮፍታሔ በዘመነ ምኒልክ በወታደራዊ ችሎታቸው የታወቁትን ሁለት ሰዎች ስምና ልዩ የጦር ክሂላቸውን ጠቅሶ፥ ወንዶችንና ሴቶችን ሳይለይ በሚቀሰቅስና ከዘመኑ ሥነልቡና ጋር በተሰናኘ መንገድ እንደ ንቃቱና ብቃቱ፥ ምኞት-ህልሙን በስንኞች ቋጠረ እንጂ የሚቾቹን የጦር መሪዎች ችሎታ ለማወደስ ሲል ብቻ ስንኞች አልደረደረም። ምናቡ ከተራው ሰው ሰበከታዊ (superficial) አተያይ የመጠቀ ሆኖ ይታያል። ስለጦር ስልተኞቹ እርሱና ዘመነኞቹ የነበራቸውን የአድናቆት አስተያየትና የእራሱን እምነት-ህልም ባጭር ስንኞች የገለፀበትን መንገድ ስናስብ የዛሬዎቹን ግጥሞች ድክመት በይበልጥ እንገነዘባለን። በ1929 ዓ.ም. ከፃፈው መዝሙር ጥቂት ስንኞች ወስደን ስንመለከትም የአድዋን ድል መቶኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የተፃፉት ግጥሞች ምን ያህል ዘርዛሪና ስድ እንደሆኑ፥ የእርሱዎቹ ደግሞ ምን ያህል ክት እና በስሜት የታመቁ እንደሆኑ እንገነዘባለን።

ድንግል ሀገሬ ሆይ ጥንተ ተደንግሎ፥ ጥ.ተ፥ ጥ.ተ፥ጥ.ተ
ህፃናቱ ታርደው ያንቺም ልብ ቆስሎ
ልጅሽ ተሰደደ አንቺን ተከትሎ፥ አ.ተ፥ አ.ተ፥አ.ተ
የህፃናቱን ደም አዘክሪ ኩሎ
እስጨነቀኝ ስደትሺ
እመቤቴ ተመለሺ

---

ኀዘንሽ መረረ እንባሽም ፈሰሰ፥ እ.ፈ፥ እ.ፈ፥እ.ፈ
በፈሰሰው እንባሽ ልጅሽ ፊቱ እራሰ

---

(ዮፍታሔ፥ የገፅ ቁጥር የለውም)።

እነዚህንና ብዙዎቹን የውድድር ግጥሞች ስናነፃፅር፥ የውድድር ግጥሞቹ ከዮፍታሔ ስንኞች አጠገብ ለመቆም እንኳ ጨርሶ የማይችሉ፥ ከሩቅ ሆነው በስርቆሽ ቢያይዋቸው እንኳ ወዲያው አንገታቸውን ደፍተው እጅ ሊነሷቸው የሚገደዱ ናቸው ማለት ይቻላል።

## 2.2 ይዘት-ቀመስ ጉዳዮች

ወደግጥሞቹ ይዘት ስንገባ በርከት ያሉ ፕሮብሌሞች እናስተውላለን። ለሁሉም ምሳሌ እየሰጡ በዝርዝር መተንተን ቦታና ጊዜ ስለሚፈጅ ዋናዋናዎቹን ነጥቦች ካጫጭር ምሳሌዎች ጋር ለማቅረብ እንሞክራለን።

### 2.2.1 ከታሪክና ከሌላ ዕውቀት ጋር ተያይዘው የመነጩ ፕሮብሌሞች

አንደኛው ፕሮብሌም ከታሪክ እውቀት መቅጠን እና ከሌሎች ዕውቀቶች ማጠጥ የሚመነጭ ነው። የአድዋን ጦርነት እና የማይጨውን ጦርነት አንድ አድርገው የሚመለከቱ ግጥሞች ጥቂት አይደሉም።

ከመቶ ዓመት በፊት
ያ ነጭ ባንዳ
ሙሶሎኒ የላከው ሀሣብ ወልጋዳ (ቁ.03፥ ገፅ 02)

እያለ ሙሶሎኒን፥ በሌለበት፥ ወደ ኢትዮጵያ ጦር ልከህል ብሎ ይሰድበዋል። ሌላው ደግሞ ስለአድዋ ጦርነት ሲያወራ፥

ያ ወራሪ ሙሶሎኒ ያ ሶላቶ
በአየር ኃይሉ ተመክቶ
በባህር ኃይሉ ተመክቶ (ቁ.29፥ ገፅ 01)

ይለዋል። የማይጨው ጦርነት፥ የየካቲት 12 የሰማዕታት ቀን፥ ቀድመው እንደተፈፀሙ ሆነው የቀረቡበት ዳርግጥምም አለ።

እልልታው ቀለጠ በመላው ትግራይ
የፋሽሽቶች እሬሣ አድዋ ላይ ሲሠጣ በፀሐይ።
ጨፍጭፋ ነበረ የአዲስ አበባን ሕዝብ፥

እስዋም በተራዋ ሆነች አድዋ ላይ የተጣለ ዝንብ፥
መጫወቻ ሆነች የውሻ የአሞራ እንዲሁም የዝንብ
(ቁ. 09፥ ገፅ 03)፡፡

ይሄ መቸም ዋናው ደፋር ዳርገጣሚ ነው፡፡ ሌላው ጓደኛው፤ "ለጥቁሮች የድል ምዕራፍ ለነጮች ግን እጅግ ሀፍረት/ተከሰተ በአድዋ የአምስት አመት ጦርነት" (ቁ 53፥ ገፅ 01) ይላል፡፡ ግጥሙ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ስለአድዋ የሚናገር ነው፡፡ ግን ጦርነቱ አምስት አመት ፈጀ ይለናል፡፡ ቀጥሎም "የጥቁሮች የድል ጮራ ፈንጣቂዋ/የአፍሪካውያን አይበገሬነት መለኪያ" እያለ የማያውቀውን ነገር በድፍረት ያሞግሳል፡፡ በስሚ ስሚ ስለልዩ ልዩ ጦርነቶች የሰማውን ሰብስቦ የደነቆለ እንጂ ስለ አድዋ አውቆ፥ አስቦ፥ አሰላስሎ፥ ስሜቱም በዚህ ታሪካዊ ሁኔታ ተነክቶ የፃፈ አይመስልም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጭፍንና ደፋር አቀራረብ በነዚህ ግጥሞች ውስጥ ብቻ የታየ ነገር አይደለም፡፡ ማስረጃ በወጉ ሳይጨብጡ ሀሳብን መንዛት፥ በጭፍን ድፍረት ዐዋቂ መስሎ ለመታየት መሯሯጥ በየመስኩ እያደር ሥር እየሰደደ የመጣ፥ አንድ ሀገራዊና ዘለለታዊ ፊደል-ቀመሶች የሚኮተኩቱት አደገኛ አዝማሚያ ነው ማለት ሳይቻል ይቀራል?

ሌላው ደጋግሞ የተከሰተ፥ ከእውቀት ማነስ ጋር የተያያዘ ስህተት ፋሽሽትንና ፋሽዝምን የተመለከተ ነው፡፡ ፋሽዝም እ.ኤ.አ ከ1922-43 ሞሶሎኒ የመራው የኢጣልያ ብሔራዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ከኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት ጋር አድዋ ላይ የተዋጉት እ.ኤ.አ በ1896 ነበር፡፡ ስለአድዋ የሚገጥሙ ብዙ ሰዎች የኢጣልያን ጦርና ሀገር "ፋሽሽት" እያሉ ይጠራሉ፡፡ ነገር ግን በአድዋ ጦርነት ጊዜ ፋሽዝም ገና ያልተከሰተ መሆኑን ጨርሶ አይገነዘቡም (ለአብነት ያህል ቁ. 19፤ ቁ. 32፤ ቁ. 30፤ ቁ. 40፤ ቁ. 09፤ ቁ. 11፤ ቁ. 12 ተመልከት፡፡ በተለይ በቁ. 19 ውስጥ ብቻ ፋሽሽት የሚለው ቃል 12 ጊዜ ተጠቅሷል)፡፡

ጦርነቱ ሲደረግ የነበሩ መሣሪያዎችንና ሰዎችን ካለማጤን የመነጩ ግድፈቶችም አሉ፡፡ "በጎራዴ ታንክ ማርከው" (ቁ. 41፥ ገፅ 02፥ ቁ. 05፥ ገፅ 06)፤ "ሮቢላ ሊያረግፈው የቦንቡን መዓት" (ቁ.16፥ ገፅ 5 እና 6) እያሉ የጣሊያን አየር ኃይል በጦርነቱ ወቅት ከሰማይ የቦንብ መዓት በአውሮፕላንና በጀት እንዳዘነመ የፃፉ ጥቂት የሚባሉ አይደሉም (ቁ.20፤ ቁ.36፤ ቁ. 05፤ ለአብነት ያህል ተመልከት)፤ ከአሉላ አባነጋ ጎን አብዲሣ አጋን ጦርነቱ ላይ ያሰለፉ (ቁ.44፥ ገፅ 03)፤ ሰኔ 27/1881 የሞቱትን ጎበናን ከገበየሁ ጎን ያሰለፉም (ቁ. 02፥ ገፅ 03) አልጠፉም፡፡

በተለይ ግጥም ቁ. 17 ደግሞ ጦርነቱን የኢትዮጵያን "አንድነት" ለማስከበር የተደረገ ፍልሚያ አድርጎ ደጋግሞ ይስላል፡፡ አፄ ምኒልክን "የአንድነት አባት" ሲል ይገልፃል፡፡ ኢትዮጵያዊው ዘማች ቋንቋ፥ ጎሳና ክልል ሳያስብ መነሳቱን፥ ፎክሮ የተመመው "ለአንድነቱ ክብር" መሆኑን፥ "በአንድነት ለአንድነት ሲዘምት ሠራዊቱ" በቆራጥነት እንደነበረ ሁሉ ተገልጿል፡፡ የቴዎድሮስ፥ የዮሐንስና የአሉላ የኢንድነት ምኞት በምኒልክም እንደቀጠለ የፃፈ ሌላ ገጣሚ አለ፡፡ ብዙዎቹ ገጣሚዎች የ"አንድነት"ን ጉዳይ እንዲህ አክርረው እንዲያንፀባርቁ የተገደዱት በዘመናቸው የፖለቲካ ሁኔታ ተጎትጉተው መሆኑ ይታወቃል፡፡ በቅርቡ ስለ አድዋ ጋዜጣ ላይ የወጡ ግጥሞችም ይህንኑ ስሜት ያንፀባርቃሉ፡፡ ስለዚህ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ አለ፡፡ በዘመቻው ወቅት "አንድነት" የሚለው እሳቤ በመሪዎቹና በሕዝቡ ቋንቋና ሥነልቡና ውስጥ ነበረ? ከነበረስ ምን ያህል ጎልቶ የወጣ ነበር? የ"አንድነት"ስ ፍቺ በወቅቱ ምን ነበር? የዘመኑ ነገሥታት፥ መሣፍንትና መኳንንት እርስ በርሳቸው ለሥልጣን የሚያደርጉትን ሽኩቻና የሀገሪቱን መወረር አነፃፅረው "ባንድ ላይ ሆነን መጀመሪያ የውጭውን ጠላት እናስወግድ" የሚል ዓይነት ነው? <u>ወይስ</u> ባለፉት ሁለት ሦስት አሥርታት የነበረውን ዓይነት የ"አንድነት" ፍቺ የያዘ ነው፡፡ ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮም የተጋጋለ የ"አንድነት" መፈክር በአማርኛ ጋዜጦችና መፃህፍት ውስጥ ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡ የዚህስ "አንድነት" ፍች ምን ነበር? ምናልባት ከጠላት መባረር በኋላ፥ በተለይ ከስደተኛነት፥ ከባንዳነት እና ከአርበኝነት ጋር የተያያዙ ሀሳቦችና ስሜቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ይብላሉ ስለነበር፥ ሀገሪቱን መልሶ የመገንባት ተግባር ደግሞ አጣዳፊ ስለነበር፥ የዚያ ዘመን የ"አንድነት" ጥሪ "ተባብረን ባንድነት ሀገሪቱን እንገንባ!" የሚል ሳይሆን አይቀርም፡፡ ቃሉ በተለያዩ ጊዜያት የነበረውንና አሁን ያለውን ፍች በጥልቀት መርምረው ስላላጤኑ የራሳቸውን ዘመን ፍቺ፥ ዘመን-ዘለል በሆነ መንገድ (anachronistically)፥ ባለፈው ዘመን ላይ ይጭናሉ፡፡ የዘመኑን ቋንቋና የዘመቻ ጥሪ ለመመልከት ቢሞክሩ ግን የተለየ ሀሳብ ያገኙ ነበር፡፡

የአፄ ምኒልክ የክተት አዋጅ ውስጥ ከተነገረው አንዳንዱን እንጥቀስ፥

---

> አሁንም <u>አገር የሚያጠፉ ሀይማኖት የሚለውጥ</u> ጠላት እግዜአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል . . . በእግዚአብሄር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም፡፡ . . . ያገሬ ሰው . . . ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ፡፡ ጉልበት የሌለህ <u>ለልጅህ</u>፥ <u>ለምሽትህ፥</u> <u>ለሀይማኖትህ</u> ስትል በኀዘን እርዳኝ፡፡...

(ገ/ሥላሴ፥ 1958፥225፥ ሥርዝ የኔ)

ከጥቅሱ መገንዘብ የሚቻለው የዘመቻው አበይት ምክንያቶች የአገር ዳር ድንበር መደፈር እና የሀይማኖት አደጋ ላይ መውደቅ ናቸው ማለት ይቻላል። ከዚህ ጋር የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን መደፈርም እንዳለበት ግልፅ ይመስለናል። ሕዝቡም እንዲዘምት የተጠየቀው፥ ያው ከርሳቸውም በፊትና በኋላም ተጠይቆ እንደሚያውቀው፥ "ለልጅህ ለምሽትህ ለሀይማኖትህ ስትል" ተነስ ተብሎ ነው። በእንደዚህ ያለ አጣዳፊና ድንገተኛ ዱብዕዳ ውስጥ ሲገባ፥ የዘመኑ ቋንቋና ገናን ሥነልቡና እርሱ ቢሆን ኖሮ ለ"አንድነትህ ተነስ!" ይባል ነበር ብለን እናስባለን።

በየካቲት 23/1888ቱ ጦርነት ላይ ስለሆነው፥ የአፄ ምኒልክ ፀሀፊ ትእዛዝ የፃፉትን ስንመረምር የኢትዮጵያን ሠራዊት የውጊያ ምክንያቶች በተዘዋዋሪ መንገድ እንረዳለን። አንዳንድ ጥቅሶች ከዚህ በታች እንዕፋለን፥

> ሠራዊቱ ስለሀገሩ ስለመንግሥቱ ተናዶ ነበርና መድፉ ይመታኛል...ብሎ ልቡ አልፈራበትም"
>
> (ገፅ 262፥ ሥርዝ ያኔ)

> "የቆሰለውም ሰው አልጋው ይቁም እንጂ ኋላ ታነሣኛለህ በመሀይምን ቃሌ ገዝቼሀለሁ ይለው ነበር።"
>
> (ገፅ 262፥ ሥርዝ የኔ)

> "ሰውም ከመንገድ ርዝመት ከተኩስ ብዛት የተነሳ ደክሞት የተቀመጠ እንደሆነ የምኒልክ ወሮታ የጮማው የጠጁ ይህ ነውን እየተባባለ እንደገና እየተነሣ ይዋጋ ነበር"
>
> (ገፅ 262፥ ሥርዝ የኔ)

በዚሁ ዕለት በዘጠኝ ሰዓት፥ የኢትዮጵያ ሠራዊት የማረከውን የጣሊያንን ወታደርና ቁስለኛውኘ ይዞ በብዛት ሲመለስ፥ አፄ ምኒልክ ግን ገና አልተመለሱም ነበር። ይህንን ያየች የእቴጌ ጣይቱ እህት ቃሏን ከፍ አድርጋ፥ "አድዋ ቤት አለህን ንጉሥህን ጠጅህን ጮማህን ትተህ ወዴት ትሄዳለህ" እያለች መለፈፏንም ገብረ ሥላሴ ፅፈዋል (ገፅ 265፥ ሥርዝ የኔ)። በጦርነቱ ላይ ለፈፀመው የጀግንነት ሙያ በዕለቱ ለፊታውራሪ ገበየሁ የተገጠመለት ግጥምም፥

> ኢጣልያ መጥቶ ታቦት የሚያረክሰው፥
> የንጉሥ ፊታውራሪ ገበየሁ ቀደሰው። ይላል
>
> (ገ/ሥላሴ፥ 266፥ ሥርዝ የኔ)

ከዚህ በላይ ከልዩ ልዩ ዐውድ አውጥተን የጠቀስናቸውን ጥቅሶች ስናጤን፥ የዘመኑ ሥነልቡናና ቋንቋ ይፈቅድ በነበረው የሠራዊት ማነቃቂያም ውስጥ ሆነ የመሪዎቹ የዘመቻ ጥሪ ውስጥ ተደጋግመው ይመጡ የነበሩት እሳቤዎች (concepts) አገር፥ አልጋ፥ ሀይማኖት፥ ጮማና ጠጅ፥ እና የምኒልክ ወሮታ ወዘተ ናቸው:: ለልጅህ፥ ለምሽትህና ለሀይማኖትህ ስትል ተዋጋም ሌላው ጠንካራ "መፈክር" ነበር ማለት ይቻላል:: በእንዲህ ዓይነት መንገድ እራሱን የሚገልፅ ዘመን ላይ ከእርሱ በኋላ የመጡ የሌሎች መንግሥታትንና የፖለቲካ ቡድኖችን "መፈክሮች" በግድ መጫን ከደራሲውም ሆነ ከአህዛቢ ታሪክ ፀሀፊዎች (popular historians) የሚጠበቅ አልነበረም:: ሕዝቡ በጀግንነትና በመስዋእትነት ያገኘውን ድል ግን፥ ተከታዩ ትውልድ ከራሱ እምነት፥ ተጋድሎ፥ መስዋእትነት፥ እና ተግባራዊ የኑሮ ልማትና እድገት ጋር እያመዛዘነ ታሪኩን ሊያበለፅግበትም ሆነ ራሱን እየሄሰ ሊያቃናበት የሚችልበትን መንገድ መመርመር ትክክለኛው ሀላፊነትና ግዴታው ይመስለናል:: እስከዛሬ የታተሙትን አድዋ-ቀመስ የፈጠራ ድርሰቶች ስንመለከት በዚህ አቅጣጫ የምናደርገው ጥረት ከፍተኛ መሆን እንዳለበት ከልብ እንረዳለን::

## 2.2.2 "ክሊሼ"-አንጋሽ ግጥሞች

"ክሊሼ" ማለት ተደጋግሞ በመወሳቱ የቸከ ሀሳብ ወይም የአነጋገር ዘየ ማለት ነው:: በመደጋገሙ የተነሣ ሊያስቀላልፍ የሚፈልገውን ሀሳብ የማያስተላልፍ እንደማለት ነው ማለት እንችላለን:: በነዚህ ግጥሞች ውስጥ ስለኢትዮጵያውያን ጀግንነት፥ ስለጣሊያን የሀገራችንን ሀብት፥ ጫሬት፥ እና ነፃነት ለመግፈፍና ለመዝረፍ መምጣት ክሊሽያዊ እና ጥራዝ ነጠቅ በሆነ መንገድ ቀርቧል::

ኢትዮጵያ፥ የጀግኖች ሀገር መሆኗ በብዙዎቹ ግጥሞች ውስጥ ተጠቅሷል:: ይህ ደግሞ በዕለት ተዕለት ወግም ውስጥ ተደጋግሞ፥ በየቀኑም ማለት ይቻላል፡ የሚነሳ ጉዳይ በመሆኑ ከግጥሞቹ ማስረጃ መጥቀስ ቦታና ጊዜ መፍጀት ነው:: ልንወያይበት የሚገባ ጉዳይ ግን አለ:: ገጣሚዎቹ የጀግኖች ተዋጊዎችን ስሞች እየጠሩ የገደሉትን ሰው ብዛት፥ የቀሉትንና የመተሩትን አንገት፥ የቀረደዱትን አንጀት፥ የገመሱትን ጭንቅላት ወዘተ. የሚዘረዝሩ ዓይነት ናቸው:: ከጀግኖቹ መሀል ጎራዴና ጦር ብቻ ይዘው ደፍረው የገቡ መኖራቸውንም የሚያወሱ ብዙ ናቸው:: በእኛ አስተያየት ግን፥ አንድ ግጥም ወይም ማንኛውም የፈጠራ ድርሰት ከዚህ አልፎ መሄድ ያለበት ይመስለናል:: እርግጥ ድርጊቶቹን መዘገቡ አስፈላጊ ነው:: ለታሪክ ፀሀፊውም ሆነ ለደራሲው፥ ለሰዓሊው፥ በጠቅላላ ለከያንያንና ለማኅበረሰቡ የሚሰጠው ግንዛቤ አለ:: ነገር ግን ዝርዝር

የዜና መዋዕልም ሆነ የሌላ ድርጊት ዘጋቢ ተግባር ነው። የገጣሚው ዋና ተግባርና ተልእኮ ተደርጎ መወሰድ የለበትም ነው የምንል። የገጣሚው ጉዳይ እነዚህ ተዋጊዎች፥ በድፍረት፥ ለህይወታቸው ሳይሳሱ ማለትም ይቻላል፥ አስደናቂ ጀብዱዎችን እንዲፈፅሙ ያደረጓቸውን ሀሳቦችና ስሜቶች በግጥሙ ማሳየት ነው። ስለ ልዩ ልዩ ጀግኖች የሚነገረውን ይዞ፥ እነዚያኑ ሀሳቦችና ቃላት ዳርና ዳር በሚገጥሙ ሆሄዎች ማቅረብ የርሱ ፋንታ ባይሆን ይመረጣል። እጀግኖቹም ሆነ እፈሪዎቹ ሀሳብና ስሜት ውስጥ ገብቶ፥ በወራሪዎቹ የኢጣልያ ወታደሮችም ይሁን በተወረሩት ኢትዮጵያን ውስጥ በጦርነቱ ወቅት የሚመላለሱትን ስሜቶች በምናቡ ጠልፎ በውብ ስንኞች ሲያቀርብ ይመስለናል ገጣሚ መሆን የሚጀምር። ይህም ብቻ አይበቃም። የማኅበረሰቡን የጀግንነት እሳቤዎችም ለማጤን፥ ለማብሰልሰል፥ ለመመርመርና ካስፈለገም ለመጠየቅና ለመሞገት መሞከርም ይጠበቅበታል። በእነዚህ ግጥሞች ውስጥ የጀግንነትን እሳቤ የሚያብላሉ፥ የሚያነሱ፥ የሚጥሉ፥ ወይም በእሳቤው ላይ የሚፈላሰሙና የሚመራመሩ ጠያቂዎች አልተገኙም። ይህ፥ ከያንያንና የታሪክ ተመራማሪዎች ሊያጤኑት የሚገባ መሠረታዊ ፕሮብሌም ይመስለናል።

ሌላው ክሊሼ ጣሊያንን ሀብታችንን፥ መሬታችንን፥ ነፃነታችንን ሊዘርፍና ሊገፍፍ መጣ የሚለው ነው። "ከድንግል መሬት ማዕድን ሊያግዝ"፥ "ጥሬ ሀብት ቦርቡሮ ሊወስድ"፤ "ነፃነታችንን ሊነጥቅ" መጣ ግን፤ የሀገራችንን ሀብቷንና አየሯን ተመኝተው እንደወረሯት እንደ ግብፆችና ቱርኮች ጣሊያንም ተሸነፈች እንጂ አልቀናትም የሚሉ ብዙ ናቸው (ለአብነት ያህል ቁ. 17ን፥ ቁ. 27ን፥ ቁ. 29ን፥ ቁ. 55ን ተመልከት)። ለዚያች "ድንግል መሬት"፥ ለዚያች "ገነት ምድር"፥ ለዚያች "ገነት ሀገር"፥ ለዚያ ሀብት የዛሬ መቶ ዓመት አባቶች መዋደቃቸውን መቶ ዓመት ሙሉ መዘመር ብቻ በቂ አይደለም። በእነርሱ ዓላማ የሚያምን ገጣሚ እነርሱ ያደረጉትን በቃላት መድገም ብቻ ሳይሆን እርሱ እራሱና ሌሎች የሀገሪቱ ሕዝቦች ባለፉት መቶ ዓመታት፥ ለዚያ ዓላማ ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖር አለመኖሩን መርምሮ በዚያ ላይ መፃፍ ነው አዲስ ሀሳብና ስሜት ያለበት ድርሰት የሚያደርገው። ጀግኖቹ ከጣሊያን ጋር ተዋድቀው ያዳኗትን መሬት ተከታታይ ትውልዶች ምን አደረጓት? ከጠላት የዳነው ሀብትስ የታለ? ምን አደረግንበት? ምን አደረገልን? ወይስ አሁንም የለ? ሀገር ከወራሪ በመዳኑ ሕዝብ በሀገሩ ምን ፈጠረ? ሀገር ከጣሊያን ወረራ በመትረፉ ሕዝብ ምን አገኘ? ካላገኘ፥ ካልፈጠረ፥ ለምን አላገኘ-አልፈጠረም?

የነፃነቱንም ጉዳይ እንዲሁ መጠየቅ ያስፈልጋል። ሕዝቡ፥ ከወረራው በፊት ምን ዓይነት ነፃነት እንደነበረው ተፍታትቶ የተገለፀ ነገር ብዙም የለም። የውጭ ወራሪን መምጣት አስከፊነት አግንኖ ይገልፃል እንጂ የሚያጣውን

ነፃነት ፈንትዎ እያሳየ፣ አንባቢን እያስጎመጀ፣ "ለካ ይህ ሊሆን ኖሯል!!" እያለ እንዲከተለው ለማድረግ ሲሞክር አይታይም። በዘመኑ በነበሩት ገዥዎችና በወራሪው መሀል ያለውን ልዩነት እያሳዩ የአንባቢን ስሜትና ሀሳብ ሲያንቀቁ አይገኙም። ለውድድሩ ግጥም ያቀረቡትም ሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚፅፉ የሀገሪቱ ታዋቂ ገጣሚዎች በተለምዶ የሚነገረውን ከማስተጋባት አልፈው፥ የሚባለውን ጠልቀው መርምረው ማኅበረሰቡን አስተውለው (ታዝበውም ማለት ይቻላል) የራሳቸውን ግንዛቤ የሚቀርፁና የሚስሉ ሆነው ብዙ ጊዜ አይገኙም። ልዩ ልዩ በዓላት ሲከበሩ ድፍን አድናቆት ወይም ድፍን ውግዘት ማዥጎድጎድ አምልኮታዊ እንጂ እውቀታዊ ሕይወት አለመሆኑን የተረዱም አይመስሉም። ነገር ግን፣ ከንቱ ውዳሴና እርግማን ስላለፈው ታሪክም ሆነ ስለዛሬው ሕይወት የሚያዝንም ከያኒም ሆነ ትውልድ የራሱን መካንነት (barenness) ለታሪክ ከመዘገብ የላቀ ፋይዳ ይሠራል ለማለት ያስቸግራል። ስለዚህ በዚህም አቅጣጫ በጥሞና ማሰብ የደራሲዎቻችን (የዜጎችም ጭምር ማለት ይቻላል) ተግባር ይመስለናል።

### 2.2.3 ዛሬን ሞጋች ይዘቶች

ከግማሽ የማያንሱ ግጥሞች የዛሬውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ አደረጃጀት እና ሁኔታ ለመተቸት የሚሞክሩ ናቸው። በቋንቋና በብሔረሰብ ላይ የተመሠረተን የፖለቲካ አደረጃጀት ገጣሚዎቹ ከ"ሚያስቡት" የኢትዮጵያ አንድነት ጋር አለመስናኘቱንና አደገኛ መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው። ይህንን ሁሉ የሚያደርጉት ስለአድዋ ድል በመፃፍ በኩል ነው። ይህንን ዓይነቱ አፃፃፍ ለአማርኛ ግጥም እንግዳ አይደለም። ቢያንስ ቢያንስ ከማይጨው እስከ ዘመነ ኢሕአዴግ ድረስ የዘለቀ ልምድ ነው ማለት ይቻላል። ጣሊያን በ1928 ዓ.ም. ሀገሪቱን እንደገና ሲወር የአድዋን ጀግኖችና የአድዋን ድል እያነሱ እነ ዮፍታሔ፥ እነ አገኘሁ፥ እነ ወልደጊዮርጊስ ሕዝቡን ለመቀስቀስ ሞክረዋል። "የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም"ም በኢምፔሪያሊዝም ላይ የተገኘ ድል ሆኖ ሲቆጠር ከአድዋ ጋር ተጣቅሷል። በሶማሌ ጦርነት ጊዜም ህዝቡን ለመቀስቀስ በጊዜው ከተደረጉት ጥረቶች አንዱ በጋዜጣና በሬድዮ ስለ አድዋ ድል ግጥሞችን ማተምና ማሰራጨት እንደነበረ የታወቀ ነው። በ1983 ዓ.ም. በሀገሪቱ ሰሜን ክፍል ጦርነት እየተፋፋመ ሲሄድም የጋዜጦች አምዶችና የሬድዮ ፕሮግራሞች የአድዋን ድል የሚጠቅሱ ግጥሞችን ለቅስቀሳ ይጠቀሙ ነበር። ባጭሩ በሀገሪቱ ውስጥ አስጨናቂና ተፈታታኝ ወቅቶች ሲከሰቱ ከፈታኙ ወቅት ጋር በቀጥታ ከመነጋገር ይልቅ ታሪክን ተገን አድርጎ ዘመኑን መሞገት የተለመደ ሆኗል (ቁ. 01፥ ቁ.02፥ ቁ.12፥ ቁ.13፥ ቁ.15፥ ቁ.17፥ ቁ. 20፥ ቁ.28፥ ቁ.34ን ለአብነት ያህል ተመልከት)።

ከሁሉም ጎሳ አድዋ መዝመቱን በተለየ ሁኔታ ለማቅረብም የጎሳዎችን ስም የሚዘረዝሩ አሉ። (ቁ.35፥ ቁ.37፥ ቁ.41፥ ቁ.47፥ ቁ.58ን ተመልከት) ለአጽንኦት ሲሉ የየብሔረሰቡን ጀግኖች ስም የሚደረድሩም አሉ (ቁ.11፥ ቁ.17፥ ቁ.34፥ ቁ.47፥ ቁ.51፥ ቁ.54 ተመልከት)።

ዘመቻው ፆታና ዕድሜ ሳይለይ መዘመቱን ብዙዎቹ ይጠቅሱና በተለይ ለእቴጌ ጣይቱ ልዩ አድናቆትና አክብሮት ያሳያሉ (ቁ. 05፥ ቁ.12፥ ቁ.19፥ ቁ.20፥ ቁ.27፥ ቁ.34፥ ቁ.42፥ ቁ.47 ተመልከት)። ጣይቱ በአፄ ኃይለሥላሴና በደርግ ጊዜ በወጡት የአድዋ ግጥሞች ውስጥ ምን ያህል ካንነው እንደወጡ በምርምር አይታወቅም። ገምቱ ብንባል ግን እንዳሁኑ አይገንኑም ወደሚለው እናዘነብላን። የዛሬው አሳሳል በእርሳቸው ላይ ያነጣጠረው ከ1966-1983 በነበረው የርእዮተ ዓለም ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል። የፆታ ጉዳይ ባለፈው መንግሥት ዘመን ተደጋግሞ ይነሳ ነበር።

ከ1983 ወዲህ ባለው ዘመን ደግሞ ሴቶች በፖለቲካና በልዩ ልዩ የአስተዳደር ሥልጣን ላይ ሲመደቡ በመገናኛ ብዙኃንም ሰፋ ያለ ጊዜ ሲሰጣቸው የታየበት ጊዜ ስለሆነ፥ ይህ ሁኔታ ጣይቱን በእነዚህ የውድድር ግጥሞች ውስጥ ከበፊቱ ጎልተው እንዲወጡ ሳይገፋፋ አልቀረም።

ገጣሚዎቹ የአድዋን ድል እያወደሱ የዘመኑን ሁኔታ ይሞግታሉ ብለናል። ይህንን ሲያደርጉ፥ ብዙ ጊዜ፥ አስጠንቃቂ ድምፅ (a voice of warning) እያሰሙ መሆኑንም መግለፅ ይገባል። ምን ማለታችን እንደሆነ ለማመልከት ጥቂት ስንኞችን እንጠቅሳለን። አንድ ገጣሚ የአድዋን ድል በከፍተኛ ደረጃ ካደነቀ በኋላ፥ በዝርዋዊ ስንኞች፥

ተተኪው ትውልድ በጎሣ ሲያምን
በእርዳታ ሰበብ ገንዘብ ሲለምን
አገሩን ሳያውቅ ክልል ሲቆጥር
አያሳዝንም? ታሪክ ሲናገር (ቁ. 17፥ ገፅ 06)

በማለት ከዘመኑ ፖለቲካ ጋር ይሟገታል። በፖለቲካው ሁኔታም አውሮፖውያን ሊደሰቱ ይገባል ባይ ነው። ምክንያቱንም ሲገልፅ፥

በጦርነቱ አልሆን ብሏቸው
በእርዳታ ሰበብ ቅኝ ገዥ ናቸው (ገፅ 07)

ይላል።

ሌላው አስጠንቃቂ ገጣሚ እንዲህ ይላል፤

ካልታደጉ በየመስኩ . . . የኛን ገድል ያስጋዋል
ዘመን ቀጥሮ ያገረሻል . . . አድዋ ሀውልቱን ያናጋዋል
እናም አድዋ አንቺም ንቂ
በድልሽ ቀን ስትስቂ
ለእግረ-መንገድ አስጠንቅቂ
ታሪክ-ምዕአት . . . ገድለ-ፋቂ
እንዳይመጣ. . . አስጠንቅቂ
የኛም ቅርስ እንደይጠፋ . . . የሞትንለት አንጡራችን
የአገር ስሜት-የጀግና ውርስ ለአድዋ ይሁን አደራችን፡፡
(ቁ.39÷ ገፅ 03)

ይህ ግጥም በአበው አንደበት ለዛሬው ትውልድ በሚመክር ድምፅ የተፃፈ ነው፡፡ ሀገሪቱ በአድዋ ያገኘችውን ክብርና ድል እንዳታጣ የሚፈራና ስለዚህም ደጋግሞ የሚያስጠነቅቅ ነው፡፡ በተለያየ መንገድ በአውሮፓ ላይ የተገኘውን ድል እየጠቀሰ በአድዋ ላይ ተዋግቶ "ጥሎ የወደቀ" ኢትዮጵያዊ የሚናገረው ተደርጎ የተፃፈው ይህ አጭር ግጥም ሥጋቱን በብዙዎቹ ስንኞች ቢገልፅም ዓላማው ማስጠንቀቅና ማትጋት ነው እንጂ ተስፋ የመቁረጥ አይመስልም፡፡ ሌሎች ወጣቱን ትውልድ የሚያስጠነቅቁ ግጥሞችም አሉ (ቁ. 45ን ለአብነት ያህል ተመልከት)፡፡ ግለሂሳዊ ድምፀቱ የጠነከረ እስከ መቶኛው ዓመት ድረስ የአድዋን ድል እየዘከረ÷ ድሉን ሳያዳብር በመቆየቱ የሚያዝንና የሚፀፀት÷ በኋለኛው (postscript) ውስጥ ጥቂት ዘርዘር አድርገን ልንመለከተው የምንወደ ግጥምም አለ (ቁ.61)፡፡

### 2.2.4 ገፀ-አድዋ

በግጥሞቹ ውስጥ አድዋ በልዩ ልዩ መልክ ተስላለች፡፡ በጥቅሉ ለሰው ልጆች በሙሉ የተስፋና ነፃነት ቤዛ ተደርጋ ትገኛለች፡፡ ድሉ÷ ኢትዮጵያን የሁሉም ዓይነት ነፃነት÷ ጀግንነት÷ ትግል÷ ወዘተ ተምሳሌት የማድረግ አዝማሚያም በግጥሞቹ ውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡ ለዚህም÷

የጉስቁል ሕዝቦች ሞገስ÷ የዓለም ነፃነት ማማ
የስብዕና ሕይወት ምንጭ÷ መብት ክብር ለተጠማ
የብርሀን ፋና ወጊ÷ ለታጋይ ሕዝቦች አርአያ
የድርብ ድል ሀሌ ሉያ÷ የጀግና ሕዝብ ታሪክ መኩሪያ
የአርነት ቋሚ ሐውልት የጀግንነት መታሰቢያ
አድዋ! ሕያው ምድር-የእናት ሀገር ኢትዮጵያ!(ቁ.41)

የሚለው ግጥም አንድ ምሳሌ ነው። በተለይ÷ በምልልስ በሚተርክ አንድ ግጥም ውስጥ የአበሻና የጥቁር ሕዝቦች አንድነት ጭብጥ ከዳርዳር ተደጋግሞ ተወስቷል። አበሻው የአድዋን ትንግርታዊ ድል የሚተርከው ለኬንያታና ለንክሩማ ነው። እነዚህ የአፍሪካ መሪዎችም ገድሉን ከሰሙ በኋላ የአበሻን ትግልና ድል ያደንቃሉ። ለነርሱም የፀረ-ቅኝ ግዛት ትግል ያለውን አርአያነት አጠንክረው ይገልፃሉ። በዚህ ግጥም ውስጥ "ጥቁር" የሚለው ቃል አንዳንዴም "መላው ጥቁር ሕዝብ" በሚል ሀረግ ውስጥ ሆኖ 16 ጊዜ ተጠቅሷል። አንዳንዶቹ ስንኞች በተለምዶ አበሾች ስለጥቁርነት ያሏቸውን አስተያየቶች ለሚያውቅ ትንሽ ያስሸረጋሉ። ለምሳሌ÷ አበሻው ለጣሊያኑ÷

ነፃነቴን ስልህ አረመኔ ካልከኝ
ሳልነካህ ሳልደፍርህ ክብሬን ከገሰስከኝ
የጥቁር መንደሬን ኢትዮጵያ እማምየን
ልውሰድብህ ካልከኝ (ቁ.38÷ ገፅ 05)

እያለ ሲናገር ሦስተኛው ስንኝ ላይ ቆም ማለታችን አይቀርም። ይህንን ስንኝ "የቴዎድሮስን÷ የዮሐንስን÷ የአሉላን ሀገር ኢትዮጵያ እማምየን..." ብሎ ፅፎ ቢሆን ግን አንገረምም ነበር። የአበሻው ጥቅል ባህርይ የሚታወቀው በዚህ መልኩ ይመስለናል። ነገር ግን አጠንክሮና እስኪያተክነው ድረስ÷ "ቆፍጣናው አበሻ"÷ ሀገሩን "የጥቁር መንደሬን ኢትዮጵያ እማምየን" ብሎ ሲገልፅ ማሰብ እንኳን የዛሬ መቶ ዓመት ቀርቶ ዛሬም የሚያስቸግረን አንጠፋም። ገጣሚው እራሱ ቢሆን ተናጋሪው ከእርሱ ግንዛቤ÷ እውቀትና ንቃት የመነጨ ይሆናል በሚል ልናደምጠው እንችል ነበር። የድምር ሀበሻ አስተያየት አስተሳሰብ እና እምነት አድርጎ ሲቀርፀው ግን÷ ምናልባት ቸር ሆነን÷ ምኞቱንና ተስፋውን ገለፀ እንልለት ይሆናል እንጂ የዘመኑን ሀሳብና ስሜት ቀረፀ ለማለት አንደፍርም።

በሌላ ግጥም ውስጥ የአድዋ ዝና አፍሪቃን÷ ካሪቢያንን÷ ደቡብ አሜሪካንን እና እስያን ያጥለቀለቀ መሆኑ እና፤ እነጋንዲ÷ ንክሩማ÷ ማርቲን ሉተርና ማንዴላም በአድዋ አርአያነት የተፈጠሩ አዲስ ጀግኖች መሆናቸው ተገልጿል (ቁ. 18÷ ቁ. 41÷ ቁ. 47÷ ቁ57)። በዓለም ላይ ተነሥቶ የነበረው የEthiopianism ትግል ተጠቅሶ ይገኛል (ቁ. 57)። ጃፓን በሩሲያ ላይ ለተጎናፀፈችው ድልም አርአያዋ አድዋ ሆና ተጠቅሳለች (ቁ. 59)።

ከዚህ በላይ እንዳመለከትነው በግጥሞቹ ውስጥ አድዋንና ጥቁር ሕዝቦችን እያያያዙ መግለፅ ተደጋግሞ ይታያል። እርግጥ ብዙዎቹ ገጣሚዎች ይህንን ግንኙነት በዕውቀትና በጥልቀት ከመግለፅ ይልቅ የጥቁር ህዝቦችን መኖርያ ሀገሮች እየጠቀሱ ለእነርሱ አርአያ ሆናለች የሚሉ ዘርዛሪና ዝርዋዊ ናቸው።

ይሁን እንጂ ሀሳቡ ራሱ መደጋገሙ አዲስ ነገር ስለሆነ ሳናወላውል ለመጠየቅ የምንገደደው ዐቢይ ጥያቄ አለ፡፡

ብዙዎቹ ገጣሚዎቻችን አፍሪካዊነትን፥ ማለትም ጥቁርነትን በእውነት* ከልብ ይቀበላሉ? ብዙ የሀገራችን ፊደላውያንና ተርታ ሕዝቦች ስለ ዘር (racial) ፖለቲካ የበሰለ ዕውቀትም ሆነ ልምድ አላቸው? ከብዙዎቹ የነቃን የምንመስል ደራስያንና ምሁር ተብየዎች አንደበትስ፥ አንዳንዴ በፊት ለፊት ድፍረትና በማን አለብኝነት፥ አንዳንዴም እያመለጠን፥ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች የመጡ ጥቁሮችን "ባሪያ! ሻንቅላ!" ስንል አንደመጥም? በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞቻችን ቡና ቤቶች፥ ሆቴሎችና ልዩ ልዩ የሕዝብ መገልገያ ሥፍራዎች የሚሰነዘርባቸውን አስተያየትስ የምናውቀው አይደለምን? በተለይ የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ነዋሪዎች አስተያየትስ ባብላጫው የማናውቀው ነውን? ታድያ በነዚህ ግጥሞች ውስጥ ተደጋግሞ የሚጠቀሰው የአድዋን ድልና ጥቁር ሕዝቦችን የማገናኘት ፈሊጥ ከየት መጣ? ከጠንካራ ባህላዊ መሠረት የመነጨ ነው? ትምህርት ቤቶቻችንና መገናኛ ብዙሀን ጥቂት የማይባሉ ኢትዮጵያውያን ስለጥቁርነት ያላቸውን የተሳሳተ አስተሳሰብ ተገንዝበው ፊት ለፊት በማስተማራቸው የተከሰተ ለውጥ ነው? በእኛ አስተያየት አድዋንና ጥቁር ህዝብን የማገናኘት ጉዳይ በነዚህ ግጥሞች ውስጥ ተደጋግሞ የታየባቸው ዐበይት ምክንያቶች የሚከተሉት ይመስሉናል፡፡

ራስን እንደ ጥቁር ሕዝብ አምርሮ መግለፅ፥ ራስን የጥቁር ሕዝብ አካል አድርጎ መሳል ለአማርኛ ሥነፅሁፍ ደራስያን የቅርብ ጊዜ ልምድ ይመስለናል፡፡ ባንድ በኩል ከ1966 ሕዝባዊ እንቅስቃሴና አብሮት ከመጣው ሰበከታዊ ማርክሲዝም-ቀመስ አስተሳሰብና፥ ከሦስተኛ ዓለምና በተለይም ከጥቁር ሕዝቦች ጋር ኢትዮጵያ አላት እየተባለ ተደጋግሞ ከሚነገረው የትግል ግንባር ቅስቀሳ ጋር ተያይዞ የዳበረ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተማሪዎች ትግል በመጠኑ የዳበረው እና በአፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን የተጀመረው፥ በኮሎኔል መንግሥቱ ይመራ በነበረው መንግስት የቀጠለው፥ ለደቡብ አፍሪካ ሕዝቦች የነፃነትና የእኩልነት ትግል ሀገሪቱ የምታደርገው ድጋፍ፥ በመገናኛ ብዙሃን ተደጋግሞ በይፋ መነገር ያስከተለው ለውጥም ሊሆን ይችል ይሆናል፡፡ በነዚህ ግጥሞች ውስጥ እንዲገኝ ያደረገው ግን በኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዮት ውስጥ የተቋቋመው የአድዋ ድል መቶኛ ዓመት በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ ለተውኔትና ለግጥም ውድድር ያወጣው ማስታወቂያ ውስጥ የተጠቀሰው አንድ መመዘኛ ሳይሆን አይቀርም፡፡

---

* የዘር ፖለቲካ ስንል የኅሳ ወይም የብሔር ብሔረሰብ ፖለቲካ የሚባለውን ለመግለፅ ሳይሆን ሰዎችን ጥቁር፥ ነጭ፥ ቢጫ ወዘተ እያለ በተለምዶ የሚመድበውን ዓይነት ፖለቲካ ለመጠቆም ነው፡፡

አንዱ መመዘኛ፥ ግጥሙም ሆነ ተውኔቱ የአድዋ ድል የነበረውንና አሁንም ያለውን ብሔራዊ፥ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ ማሳየት እንደሚገባው የሚጠቁም ነው፡፡ በየትም በኩልና ምክንያት ይምጣ፥ እየዳበረ እስከቀጠለ ድረስ ይህ ለውጥ እንኳ የሚያስደስት ለውጥ ነው፡፡

## 3. ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ በግጥሞቹ ውስጥ ያስተዋልናቸውን ከአፃፃፍ እና ከይዘት-ቀመስ ጉዳዮች ጋር የተያያዙትን ዐበይት ፕሮብሌሞች ለማመልከት ሞክረናል፡፡ አፃፃፍን በተመለከተ ገጣሚዎቹ ግጥም መፃፍን በስንኞች መጨረሻ የሚመጡ ሆሄያትን እንደምንም ብሎ የማገጣጠም (ያውም፥ ብዙ ጊዜ ለጆሮ ሳይሆን ለዐይን) ሥራ አድርገው የተቀበሉ ይመስላል፡፡ የላሸቁ ዘይቤዎችን መልሶ ማላሸቅ፥ የዘመንንና የቋንቋን ግንኙነት አለማስተዋል፥ የቦታዎችንና የሰዎችን ስሞች ያላንዳች ቴክኒካዊ ፋይዳ መደርደር እና ተራኪ ትረካን በስድ ንባባዊ ስንኞች ማቅረብ ብዙዎቹ ውስጥ ጎልቶ እንደሚታይ ባጭርጭሩ አመልክተናል፡፡ ይዘታቸውም ቢሆን በተለምዶ ዘለለታዊ ጨዋታ በመገናኛ ብዙሀን የሚቀርቡትን ተደጋጋሚ እሳቤዎች እንደ ከያኒ ጠልቆ ከመመርመር ይልቅ መልሶ ማስተጋባትን የመረጡ ይመስላል፡፡ በዚህ ክሊሼያዊነታቸው ላይ ስለሚዕፉበት ርእስ በቂ ዕውቀትን ከታሪክ መዛግብት፥ ከትውስታዎች፥ ከትርክቶች ቀስሞ ጥበባዊ በሆነ መንገድ ስሜታቸውን ለመግለፅ በቂ ጥረት አለማድረጋቸው ስለታከለ ግጥሞቻቸውን አድክሞባቸዋል፡፡ የአድዋን ድል ተገን አድርገው ዘመነኛውን ፖለቲካ ሲሞግቱም በሰበካው እንጂ ብዙም አይጠልቁም፡፡

ምናልባት፥ ለዚህ ሁሉ ረግረግነት አንዱ ዐቢይ ምክንያት፥ ብዙዎቹን ግጥሞች ያነቃቃቸው ከመንፈስ-ድርሰት ይልቅ መንፈስ-ሽልማት ሆኖ ይሆናል፡፡ በተቻለ መጠን በሳል፥ ጥልቅና ውብ የሆኑ ግጥሞችን ለማግኘት ታስቦ የተመደበው ማትጊያ፥ ባልታሰበ መንገድ፥ ብዙ ጀማሪ ደራስያን፥ ዕድላቸውን እንዲሞክሩ ገፋፍቷቸው ይሆናል። የጊዜው ማጠሩና የራስ-ስንሰራ (self-censorship) አበሳ ደግሞ ትብ ብእር ያላቸው ገጣሚዎች እንዳይሳተፉ ሳያደርጉዋቸው አልቀሩም፡፡ ብቻ በሦስት ነገሮች መፅናናት ይቻላል፡፡ አንደኛው፥ ለውድድር ከቀረቡት ገጣሚዎች መሀል አምስት ያህሉ ተስፋ የሚጣልባቸው መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው፥ በተለይ የግጥም ቁጥር 61 ደራሲ ከሁላቸውም በላይ ጎልቶ የወጣ ብእረ-ትብ፥ ለመፈላሰፍ የሚሞክር፥ ስሜተ-ንቁ ደራሲ መሆኑ ነው፡፡ ሦስተኛው፥ በውድድሩ ላይ የተሳተፉት ገጣሚዎች በዚህ መጣጥፍ ውስጥ ያነሳሳናቸውን ነጥቦች መርምረው፥

ብእራቸውን አቃንተው፥ የማስተዋል አቅማቸውን አዳብረው፥ እውቀታቸውን አሳድገው ይጽፋሉ ብለን ተስፋ ማድረጋችን ነው

## 4. ኋለኛ (Postscript)

### ግጥም ቁ. 61

ግጥሙ የአድዋን ድል ታላቅነት ያደንቃል፡፡ በዚህ ከሌሎቹ የውድድር ግጥሞች ጋር ይመሳሰላል፡፡ ልዩነቱ ግን ሲያደንቅ በውብ ዘይቤዎች በተቋጠሩ ስንኞችና አርኬዎች መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ዐቢይ ልዩነት፥ ወደል ወደል ጥያቄዎችን ማንሳቱና፥ በሀሳብና በስሜት ሞገድ ውስጥ እየተመላለሰ አዝኖ የማሳዘን፥ ተሸብሮ የማሸበር ኃይል ያላቸው ስንኞች የሚገኙበት መሆኑ ነው፡፡ አንዳንዴ ራሱንና የዘመኑን ሰው ይሄሳል፡፡ ሲሄስ ግን ጭካኔ በተሞላበት ምሬት ሳይሆን የህዝቡን አቅምና ሁኔታ እያስተዋለ፥ ለመረዳትም እየሞከረ፥ በርሕራሄና በመቆጨት መልክ ነው፡፡ መቆጣት የሚሻውን ያህል ወይም ከዚያም በላይ ይራራል፡፡ የዚህ ሁሉ መሠረቱ የግጥሙ ተስፋ-ጠገብ (optimistic) መሆን ይመስላል፡፡ ገጣሚው፥ በዘመኑ ሁኔታ እንደሌሎቹ ተስፋ ያልቆረጠ፥ የአድዋን አርአያነት ተከትሎ ማኅበረሰቡን አሻሽሎ ማነፅ ይገባል የሚል ነው፡፡ ጥልቅ በሆኑ ተፈላሳሚ ስንኞችም ተመራምሮ ያመራምራል፡፡ አንዳንድ የግጥሙን ኋልቶች (qualities) ከግጥሙ ምሳሌዎች እየጠቀስን ለማብራራት እንሞክራለን፡፡ ከዚያ በፊት ግን ስለግጥሙ ፍሰት (flow) ያስተዋልነውን እናስረዳለን፡፡

ግጥሙ መሠረታዊ የፍሰት ፕሮብሌም ያለው ይመስለናል፡፡ የፍሰት ስንል በግጥሙ ውስጥ የተገለፁ ጉዳዮችንና የአርኬዎችን ቅደም ተከተል መጠበቅ አለመጠበቅ ማለታችን ነው፡፡ የአድዋን ድል በማድነቅና የ"ትንግርቷን' ምሥጢር በመመርመር አንድ ገፅ ያህል ከሄደ በኋላ ስለዘመቻውና ስለአውሮፓ መኅምጀት ሲናገር የአንባቢን የስሜት አካሄድና የመከታተል ፍላጎት ሳያደናግር አይደለም፡፡ ከዚያ እስከ ገፅ ሦስት መጨረሻ ገደማ ስለአድዋ ዘመቻና ድል በውብ ቋንቋ ግን የሀሳብና የስሜቱ ፍሰት በቀና ሰንሰለት ከአርኬ ወደ አርኬ ሳይዛመት ይቀጥላል፡፡ "የብርሀን ጎህ ቀደደ፥ የነጻነት ማሾ በራ" ይልና በጊዜያዊ የዜማ ለውጥ ወደ ዛሬው ዘመን ይሸጋገራል፡፡ ከዚህ ስንኝ ጀምሮ ግጥሙ እስኪፈፀም ድረስ የአድዋን ድልና የዛሬውን ኢትዮጵያዊና አፍሪካዊ ሁኔታ ሊመለከት ይሞክራል፡፡ ለየስንኞቹና ለየአርኬዎቹ መለያ ቁጥር ሰጥቶ፥ ሳያስፈልግ የተደጋገሙትን ለይቶ፥ ቅደም

ተከተላቸው ቢስተካከል ይበጃል የሚባሉትን አስተካክሎ አሳይቶ፤ የገጣሚውን የኅሊና ሞገድ አኪያሄድ እያሳዩ ግጥሙን በጥልቀት መተንተን ያስፈልጋል። ግጥሙም ይህ ትኩረት ይገባዋል። ስንጣደፍ ያልፈፀምነውን፥ ከዚህ በላይ ግን የጠቆምነውን ዝርዝር ትንተና አንድ ጎበዝ ሀያሲ ሲያያዘው በቅርቡ ለማየት ተስፋ እናደርጋለን። ለጊዜው ግን አንዳንድ ስንኞችንና አርኬዎችን እየጠቀስን ከፍ ብለን በጥቅሉ ያወጅነውን የግጥሙን ውበት እናብራራለን።

ጣሊያንና አውሮፓ አፍሪካን ለመቀራመት ምን ያህል እንደጓጉ ሲገልፅ፥

ያወሮፓ መንጋጋ ታየ፥ ስታዛጋ አፏን ከፍታ፥
ወስፋቷ ጩኸት አሰማ፥ የምግብ ያለህ ኡኡታ፥
አይኖቿ ተቁለጨለጩ፥ ጎመዠች አፍሪካን አይታ፤ (ገፅ 02)

ይላል። ሌሎቹ ገጣሚዎች በዘርው ዳርግጥም ማዕድናችንን፥ መሬታችንን፥ ሀብታችንን ልትዘርፍ ተስገበገበች፥ ተጣደፈች እያሉ የሚዕፉትን እርሱ መስገብገቧን መንጋጋዋ እስኪታይ አፏን ከፍታ በማዛጋትዋ፥ በምግብ ያለህ እሪታዋና በሆዷ መንጓጓት፤ ያየችውን ሁሉ ለመንጠቅ ያላትን ፍላጎት በሚቁለጨለጩ ዓይኖቿ ገልፆታል። በዚህ ዓይነት ቋምጣ ጦሯን ሰብቃ ከንፋ አፍሪካ ስትገባ ተቃውሞ የሚያጋጥማት ከተለያየ አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ነው የቀረበው።

ምጽአታዊ ምልኪ ታየ፥ አበው ድንገት ተሳቀቁ፥
ያንቀላፉ አራዊት ባነው፥ ከየጉድጓዳቸው ነቁ፤
የመቃብር አፎች ጮኸው፥ በሟርት ሳቅ አወኩ
ጉጉቶች ጓጎሩ፤ ውሾች አላዘኑ፤ ተኩሎች አለቀሱ
ተራሮች ራዱ፤ ቀላያት ተናዱ፤ አድባራት ፈረሱ። (ገፅ 02)

የጣሊያን መምጣት ከአስፈሪው የምጽአት ቀን ጋር ተጣቅሷል። በ'ምጽአቷ' ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ተፈጥሮ በሙሉ ነው የሚያዝን የሚያነባ። ሙታን ሳይቀሩ የመቃብሩን አፍ ፈንቅለው በተቃውሞ ይጮህሉ። እንስሳትና አራዊት፥ ድንጊያዎች፥ ተራሮች ሁሉ ይረበሻሉ፥ ይጮህሉ፥ ይታመሳሉ። ገጣሚው፥ በምናቡ ወደኋላ ተጉዞ የጣሊያን ወረራ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያስከተላቸውን ልዩ ልዩ መናጋቶች ለመሳል ሞከረ እንጂ በተለምዶ እንደሚያደርገው የጦርነቶች ሰለባ የሚሆኑትን የሰዎችን ሁኔታ ብቻ አልሳለም። በዚህም በአንባብያን ላይ የሚኖረውን ስሚታ (effect) ያበለፀገ እና ክስተቱንም ለየት ካለ ማዕዘን (angle) ለመመልከት የሞከረ ይመስላል (ለማንፀሪያ፤ ፈቃደ፥ 1984፥ 83-85 ተመልከት)። የወራሪውን ጦር ከገለፀበት ሁኔታም፥

ምድርን የሚያናጉ፥ ረግጠው የሚቀርፉ፥ መቶ ሺህ ጫማዎች፥
አፍሪካን ረገጡ፥ አሲዳም እግሮች፥ የጎልያድ ኮቴዎች
ግዙፍ ሸሆናዎች፥ የብረት ዱካዎች (ገፅ 03)

የሚሉት ስንኞች ይገኛሉ፡፡ የገጣሚው መራር ጥላቻ፥ የጦሩ ብዛት፥ እና ጦሩ አገርና ሰው ለማጥፋት ያለው ችሎታ በተለያዩ ዘይቤዎች በቀላሉ ተገልፀዋል፡፡ ተራ ስድብ ሲሳደብ አናገኝም፡፡

ከብዙ ምጥና ትግል በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ማሸነፉን 'የብርሀን ጎህ ቀደደ የነፃነት ማሾ በራ" በሚለው ስንኙ ከከፈተ በኋላ ነው ግጥሙ የጥንቱንና የአሁኑን እያጣቀሰ ከበድ ከበድ ያሉ አስተውሎቶችን ለመሰንዘር የሚሞክረው፡፡ መቶኛውን የአድዋ ድል በዓል ለማክበር እና በድሉ ለመኩራት መዘጋጀቱን ገልፆ አፍታም ሳይቆይ ራሱንና ዘመኑን እንዲህ እያለ ይታዘባል፥

ለክብርሽ ዝክር ለመቆም፥ አቅም ሳይኖረው አቅማችን፥
ሚዛኑ ላይ እንደሚቀል፥ ገፀ በረከት፥ ስጦታችን
በመሰዊያው ላይ ኮስሶ፥ እንደሚያሳጣን መስዋዕታችን
እየፈራን፥ እየሰጋን፥ እያወቀው ልቦናችን፤
በጮራራ፥ በቀራራ፥ በኮሳሳ ተዳፈርኛሽ፥
በራቀን ፍሬ ተስፋ ቆርጠን በደረስንበት ቀረብንሽ፥
ያበደርሽንን ውድ መክሊት፥ ሳናተርፍበት ቆየንሽ (ገፅ 3-4)

በዓሉን ለማክበር የተነቃቃው መንፈሱ ድንገት ጥያቄ ያነሳል፡፡ የአድዋ ድል ባስገኘው ታሪካዊ ክብር ላይ የጨመርነው የለንም፤ ድሉን በልዩ ልዩ ማኅበረሰባዊ ድሎች አላሳደግነውም፥ አላበለፀግነውም፡፡ ስለዚህ በዓሉን ለመዘከርና ለማክበር አንችልም ባይ ነው፡፡ ምክንያቱም፥ ገጣሚው፥ ይበዛብናል፥ ይከብደናል፥ አንመጥነውም ብሎ ያምናልና፡፡ ማኅበረሰቡ የተሰጠውን "መክሊት" ሳያተርፍበት የቆየ ስለሆነ፥ የእርሱም ስጦታ "ጮራራ፥ ቀራራ፥ ኮሳሳ" ስለሆነ ቢያከብርም እያፈረ፥ አንገቱን ደፍቶ ነው የሚል ብጤ ነው፡፡

ባናክልም ያንቺን መጠን፥ ባንገዝፍም እንዳንቺ ግዝፈት
ሙሉ ነውና ልባችን፥ በፍቅርና በእምነት (ገፅ 04)

ሲልም ከአድዋ ድል ባለቤቶች፥ ተዋግተው ድሉን ካስገኙት የዚያን ዘመን ሰዎች ጋር እኩል የሚያስቆም ገድል የለንም ማለቱ ነው፡፡ የእርሱ ዘመንና ትውልድ ግን ለአድዋ ፍቅር ያለውና በአድዋም የሚያምን፥ የአድዋን ድል

የሚዘምር፥ እንጂ የራሱ የሆነ ትልቅ የድልም ሆነ የሥራ ሀውልት እንደሌለው የሚጠቁምም ይመስላል። ይህ የራስ ትዝብትና የራስ ወቀሳ ግን መርሮ አይመርም። ገጣሚው፥ በራሱም ሆነ በትውልዱ ጨከኖ አይጨክንም። ስለዚህም አድዋን ይማፀናል፥ ይቅርታ ይጠይቃል፥ "ይቅር በይን አድዋ አንቺ የድል ጣኦታችን..." እያለ። በልመናው ወቅት እንኳ የእራሱን የበታችነት አይዘነጋም። ባንድ በኩል ህዝቡ የአድዋን ድል እያደነቀ፥ በስምዋ "ቀን ከሌት እየተራበ፥ ሽንብራ ይቆርጥምበት" ብሎ ብሶቱን በስላቅ የሚስልበት፤ በሌላ በኩል ደግሞ፥

በመርገጫሽ ይስገድበት፥ ስምሽን ጠርቶ ይማልበት
ሁሌም ለዝንተ ዓለም ለነጻነት ይጣርበት (ገፅ 04)

ትናንት ህይወቱን እንዳኖራት፥ ተከትሎ ያንቺን ፋና
ነጻነቱን እንዳገኛት፥ ከእሾህ ከቆንጥር ጎዳና
እስቲ ዛሬም ይፈልጋት፥ ለስምሽ ሰጥቶ አዲስ ቃና
ሀይለኛ ማስገበሩን፥ ጉልበተኛ መናጠቁን፥መቼም
አይተውምና (ገፅ 04)።

እያለ፥ አድዋን ዘለዓለማዊ የነጻነት ትግል አርማ እንዲያደርጋት የሚማጠንበት ጊዜ አለ።

ጥሪው ለአዲስ ዓይነት ነፃነት ይታገል የሚል ዓይነት ነው። ኢትዮጵያዊውም ሆነ አፍሪካዊው ባጠቃላይ፥ ዛሬ ይዞት የሚገኘውን ነፃነት፥ ገጣሚው፥ እንደቅርፃዊ ነፃነት እንጂ፥ ሥጋ፥ ደም፥ አጥንት ኖሮት ህያው እንደሆነና፥ ቁምነገራዊ ይዘት እንዳለው ነፃነት አድርጎ አይመለከተውም። ላይ ላዩን የሚታኝ አብረቅራቂ ጌጥ እንጂ የሚጨበጥና የሚዳሰስ ዋጋና ይዘት ያለው አይደለም ባይ ነው።

እንደማይመክት ልል ጋሻ፥ እንደማይደግፍ ለጋ ባላ
ለወግና ለጌጥ እንጂ፥ ለሙቀት እንደማይለብሱት፥ ጥበብ ኩታ
ነጠላ አፍሪካዊ እርነቱ አለባትና ሰሀ፥...(ገፅ 04)

የሚሉት ስንኞችና በዚህ በ22ኛው አርኬ ውስጥ ያሉት ሌሎች ስንኞች ይህንኑ የነፃነቱን ቀፎነት የሚገልፁ፥ ጠላቶቹ ዛሬም በስውር ሁለመናውን አስረውት እንደሚገኙ የሚያሳዩና እሱ ግን መታሰሩን ገና ስላላወቀ ነፃነቱን እያወደሰና እያቅራራ በባዶ ሆዱ ድሉን ያገሳል የሚሉ ናቸው። አያቶቹ በአድዋ ድል ያደረጓቸው የጠላቶቹ ወገኖች ደግሞ፥ በተለያየ ዘዴ ነጻነቱን እንዳሳጡትና በባዶ ጩኸቱም እንደሚሳለቁ፥ በጦርነት ማግኘት ያቃታቸውንም በስውርና

በረቂቅ ስልት ለማግኘት እንደሚጣደፉ አለመገንዘቡንና መደንዘዙን በሀዘን ይጠቅስና፥ ለዚህም አድዋ ይቅር እንድትለው ገጣሚው ይለምናታል። "ከድንዛዜው ቀስቅሰሽ፥ ከአዚም ባህር መንጥቂው" እያለም ይማፀናታል።

በሚጋጩ፥ በሚቃረኑ ተግባራት እራሱን ተብትቦ እንደሚኖር፥ የራሱ ኑሮ ለራሱ የማይፈታ ዕንቆቅልሽ ሆኖበት እንደሚናውዝ፥

በነጻነት አቀርቅሮ፥ ባገም ጠቀም ተፍገምግሞ፥
በሳቅ ለቅሶ ሲነፋረቅ
በለቅሶ ሳቅ ሲንሰቀሰቅ
በመጽዋቾች ማቅ ስላቅ፥ ኩራት እራቱ ስትማቅቅ
በመሆን ወይም ባለመሆን፥ በቁርጥ እውነት ሽምቀቆ
እየኖረ ባለመኖር፥ በሕይወት አያዎ ታንቆ

(ገፅ 05፥ ሥርዝ የኔ)

በሚሉት ስንኞች እየገለፀ፥ በድል አለመልማቱ አላንስ ብሎት፥ እራሱን ለሌላ ዓይነት ባርነት ማጋለጡንም እንደሚከተለው ያቀርባል።

በነጻነቱ መደብ ላይ መሸማቀቅ መሳቀቁ
-----------------------------------
የሰለለ ደቂቅ ድርሳን
በምጽዋት እንጉርጉሮ፥ በርጥባን ዜማ ማረቁ፤

እያሉ በሚሄዱ ስንኞቹ አዲሱን የተመጽዋችነት ባርነቱን፥ የባለሙያ (professional) ለማኝነቱን በሀዘን ይከትባል።

ባጭሩ፥ የዚህ ገጣሚ ህሊና በማዕበል ውስጥ ሆኖ የሚሰቃይ፥ ያድነው በመሰለው ተስፋ ላይ ሁሉ ለመንጠልጠል እና ለመዳን የሚሻ፥ ያለበት ሁኔታ ደግሞ አሳፋሪ፥ አሳዛኝና አንገት የሚያስደፋ ሲሆንበት የሚባባ፥ የሚቃትት፥ የሚትከነከን ነው። እንደ ብዙዎቹ የውድድር ግጥሞች ግልብ እና ላይላዩን ብቻ የሚፎክር ጋዜጣ-ሬድዮ አይደለም። ከራሱ ሀሳብና ስሜት ጋር የሚታገል ዓይነት ነው። እነዚህ ውስጣዊ የስሜትና የሀሳብ እንፋሎቶች እውስጡ እየተሯሯጡ፥ አንዳቸው ካንዳቸው ልቀው የበላይ ለመሆን ተራ በተራ ሲሽቀዳደሙ ስንኞቹ ያሳያሉ። ቀደም ተብሎ እንደተጠቀመው፥ ግጥሙ፥ ከዚህ የቅምሻ ሂስ የላቀ ዝርዝርና ጥልቅ ትንተና ያስፈልገዋል።

# ጥቅስማ (References)

## የአማርኛ ምንጮች

ስድሳ አንዱ ግጥሞች ከቁ. 01-61 ተኮድደው (coded) በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ውስጥ ይገኛሉ።

ከበደ ሚካኤል፥ ታሪክና ምሳሌ፥ አዲስ አበባ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ 1935።

ዮፍታሔ ንጉሤ፥ "አፋጀሽኝ"፥ ጥቅምት 1958፥ አዲስ አበባ። የገፅ ቁጥር በሌላቸው ሁለት የመጨረሻ ቅጠሎች ውስጥ። በስቴንስል ተቀርፆ የተባዛ።

ፀሀፊ ትእዛዝ ገ/ሥላሴ፥ ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት አዲስ አበባ፥ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ 1959።

መንግሥቱ ለማ፥ ባሻ አሸብር በአሜሪካ፥ አዲስ አበባ፥ ቼምበር ማተሚያ ቤት፥ 1967።

ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፥ ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት፥ አዲስ አበባ፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ 1983።

ፈቃደ አዘዘ፥ "የአፍሪካ ጥሪ (ለአህጉር ገንቢዎች)"፥ ውይይት፥ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማህበር መጽሔት፥ 3ኛ ሴሪ፥ ቅፅ 1፥ ቁጥር 1፥ መጋቢት 1984፥ ገፅ 83-85።

ዮሐንስ አድማሱ፥ "ለማስታወስ ያህል - ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ"፥ መጀመሪያ በመነን፥ ሰኔ/1961፤ ገፅ 20-23 እና 28፥ አሁን በፈቃደ አዘዘ፥ የስነፅሁፍ ሂስ ምንጭ፥ መድበል 02 (1951-1961)፥ ጥቅምት 1985፥ ገፅ 204። ያልታተመ። ጥቀሱ የተወሰደው ከፈቃደ መድበል ነው።

## የእንግሊዝኛ ምንጮች (በተጠቀሱበት ቅደም ተከተል)

Belinisky, Vissarion. "Vissarion Belinisky: A Russian Contemporary Looks At Scott", in John O.Hayden (ed.), *Scott: the Critical Heritage*. Routledge & Kegan Paul, 1970.

Lukacs, Georg. *The Historical Novel*. London: Merlin Press, English translation, 1962.

Grierson, Herbert (Sir). "History and the Novel" in *Sir Walter Scott Lectures 1940-1948*, with an introduction by Professor W. L. Renwick. Edinburgh at the University Press, 1950.

*Macaulay's Miscellaneous Writings*. London, Longman, Green and Co., 1889.